21ኛ ዓመት ቁጥር 14
21th Year No. 14

ባሕር ዳር ….. ቀን 2008 ዓ.ም
Bahir Dar, ….., 2016

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

**Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State**

✉ *1324*
ያንዱ ዋጋ......ብር
Unit Price Birr…..

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር 239/2008 ዓ.ም**

**የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ማቋቋሚያና ማስተዳደሪያ አዋጅ**

**Content**

**Proclamation No. 239/2016**

**The Amhara National Reginal State Irrigation Water Users' Associations Establishment and Administration Proclamation**

## አዋጅ ቁጥር 239/2008 ዓ.ም

***በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራትን ለማቋቋምና ለማስተዳደር የወጣ አዋጅ***

## Proclamation No. 239/2016

**A Proclamation Issued to Provide for the Establishment and Administration of Irrigation Water Users' Associations in Amhara National Regional State**

በክልሉ ውስጥ በመስኖ እርሻ የውሃ ሀብትን በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ለምግብ ዋስትናና ለኢኮኖሚ ልማት መረጋገጥ የላቀ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው በመታመኑ፤

WHERE AS, it is believed that making use of water resources for agricultural irrigation properly has potential contribution to food security and economic growth in the Region;

በአርሶ አደር ደረጃ ለሚመሩ የመስኖ እና የድሬኔጅ ሥራዎች ተስማሚ የሆነ የሕግ ማዕቀፍ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

WHERE AS, it is necessary to put in place compatible legal framework for farmers' management of irrigation and drainage systems;

በገጠሩ አካባቢዎች ለትርፍ ሳይሆን ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩና ለሕዝብ ጥቅም የመስኖና የድሬኔጅ አገልግሎቶችን የሚሰጡ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት የሚደራጁበትን ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

WHERE AS, it is necessary to establish a system for the formation of self –regulating non- profit oriented irrigation water users' associations that act in the public interest to provide irrigation and drainage services in rural areas;

በክልሉ መንግስት፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እና በህብረተሰቡ ወጪ የተገነቡ እና የሚገነቡ የመስኖና ድሬኔጅ አውታሮችን ለማኅበራት ማስተላለፍ የሚያስችል የሕግ መሠረት በመጣልና በማኅበራቱና በአገልግሎት ሰጪዎች መካከል ያለውን የአገልግሎት አቅርቦት በመቆጣጠር የተሻለ የውሃ ሀብት አስተዳደር ስርዓት የመዘርጋቱ አስፈላጊነት ስለታመነበት፤

WHERE AS, it is believed that it is necessary to establish a legal basis for the transfer of irrigation and drainage system's constructed and to be constructed by the regional government, non- governmental organizations and the society funds to associations and to regulate supply of services between associations and service providers to achieve improved management of water resources;

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ /49/ንዑስ አንቀጽ 3 (1) ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara Region, pursuant to the powers vested in it under Article /49/, sub-article 3/1/ of the Revised National Regional Constitution, hereby issued this proclamation.

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

## PART ONE
## GENERAL

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ *"የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት ማቋቋሚያና ማስተዳደሪያ አዋጅ ቁጥር 239/2008 ዓ.ም"* ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 1. Short Title

This proclamation may be cited as the "Irrigation Water Users' Associations Establishment and Administration Proclamation No 239/2016."

### 2. ትርጓሜ

1. የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

ሀ/"ማኅበር"ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በክልሉ ውስጥ የተደራጀና የተመዘገበ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበር ነው፤

### 2. Definitions

1. Unless the context otherwise requires, in this proclamation:

a/ "Association''means an irrigation water users' association established and registered in the region, in accordance with this proclamation;

ለ/ "የመስኖ እና የድሬኔጅ አውታር" ማለት ወደ ተወሰነ መሬት አካባቢ የመስኖ ውሃን ለማጓጓዝ ጥቅም ላይ የሚውል ቦይ ወይም የቱቦዎች ወይም የመስኖዎች አውታር ሲሆን ከእነዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ማንኛውንም የውሃ መጥለፊያን፣ ግድብን ወይም የውሃ ማግለያ ውቅርን፣ ማጠራቀሚያን ወይም ኩሬን እንዲሁም ማናቸውንም የመስኖ ውሃ መተላለፊያ በሮች፣ ፖምፖችን፣ መሬትን፣ ሕንፃዎችን፣ መሣሪያዎችን፣ መጋቢ መንገዶችን፣ እንዲሁም የመስኖ አውታሩን ከነድሬኔጁ ጥቅም ላይ ለማዋል፣ ለመጠገን ወይም ለማደስ አስፈላጊ የሆኑ ውቅሮችን ሁሉ ያጠቃልላል፤

ሐ/ "የአገልግሎት ክልል" ማለት ማኅበሩ የሚገለገልበት የተወሰነ የመሬት ክልል ነው፤

መ/ "የውሃ አቅርቦት መገኛ ቦታ" ማለት አንድ ማኅበር ለመስኖ የሚውል ውሃን በኃላፊነት ማስተዳደር የሚጀምርበት የውሃ መገኛ ቦታ ሲሆን የውሃ ግድብን፣ መጥለፊያን፣ የማግለያ ውቅርን፣ በዋናው የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ውስጥ የሚገኙ በሮችን ወይም ውሃ ማስተላለፊያዎችን፣ ካናልን፣ የውሃ ጉድጓድን፣ ምንጭን ወይም የፓምፕ ጣቢያን ሊያካትት ይችላል፤

ሠ/ "ዘመናዊ የመስኖና ድሬኔጅ አውታር" ማለት በመደበኛ ጥናትና ዲዛይን ላይ በመመስረት የተገነባ ወይም ዘመናዊ እንዲሆን የተደረገ የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ነው፤

ረ/ "ባህላዊ የመስኖና ድሬኔጅ አውታር" ማለት አርሶ አደሮች በልምድ ያካበቱትን ዕውቀትና በአካባቢ የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የገነቡት የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ነው፤

b/ "Irrigation and drainage system" means a canal or a system of canals or pipes that can be used to transmit water to a defined land area for irrigation including any associated weir dam or diversion structure ,storage reservoir or pond as well as any gates, pumps, land , buildings, equipments, access roads and structures which are necessary to operate , maintain and repair the system together with any associated drainage canals;

c/ "Service area" means the defined land area where the association operates;

d/ "Water supply point" means a point at which an association takes responsibility for the management of irrigation water which may include a dam or weir, a diversion structure, a gate or turn-out in a main irrigation and drainage system, a canal , a hydrant, a well, a spring or a pumping station;

e/ "**Modern irrigation and drainage system**" means an irrigation and draiinage system constructed on the basis of a formal study and design or a modernized irrigation and drainage system;

f/ "Traditionl irrigation and drainage system" means an irrigation and drainage system constructed by farmers using their own indigenous knowledge and locally available materials;

ሰ/ **"አሀድ"** ማለት የአንድ ማኅበር የአገልግሎት ክልል የተወሰነ ክፍል ነው፤

ሸ/ **"ጠቅላላ ጉባኤ"** ማለት የአንድ ማኅበር ከፍተኛ የውሳኔ ሰጪ አካል ነው፤

ቀ/ **"የሥራ አመራር ኮሚቴ"** ማለት የአንድን ማኅበር የሥራ እንቅስቃሴ እንዲከታተልና እንዲቆጣጠር በጠቅላላ ጉባኤው የተመረጠ አካል ነው፤

በ/ **"ዋና የመስኖና ድሬኔጅ አውታር"** ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ወደሆኑ የማኅበራት የአገልግሎት ክልሎች የመስኖ ውሃን ለማጓጓዝ የሚያገለግል የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ነው፤

ተ/ **"ፌዴሬሽን"** ማለት የዋናውን የመስኖና የድሬኔጅ አውታር የማስተዳደርና የመጠገን ኃላፊነት ያለበትና በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ የውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት ፌዴሬሽን ነው፤

ቸ/ **"አገልግሎት ሰጪ"** ማለት ከፌደሬሽኑ ሌላ ዋና የመስኖና ድሬኔጅ አውታርን የማስተዳደር፣ የማሠራትና የመጠገን ሥራ የሚያከናውን ማናቸውም የመንግስት ወይም የግል ድርጅት ነው፤

ኀ/ **"ቢሮ"**ማለት የክልሉ ውሃ፣ መስኖና ኢነርጅ ልማት ቢሮ ነው፤

ነ/ **"የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት መዝገብ"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ/36/ንዑስ አንቀጽ /1/ ፊደል ተራ ቁጥር /መ/ መሠረት በቢሮው የሚያዝ መዝገብ ነው፤

ኘ/ **"መተዳደሪያ ደንብ"** ማለት በዚህ አዋጅ እና ቢሮው በሚያወጣው የአደረጃጀት መመሪያ መሠረት ከተዘጋጀ በኋላ በማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ፀድቆ እና ለቢሮዉ ቀርቦ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ በሥራ ላይ የሚውል ደንብ ነው፤



g/ "**Unit**" means a defined part of the service area of an association;

h/ "**General assembly**'' means the supreme decision making body of an association;

i/ "**Management committee**" means the body elected by the general assembly to oversee and supervise the activities of an association;

j/ "**Main irrigation and drainage system**" means an irrigation and drainage system that can be used to transmit water to the service areas of two or more associations;

k/ **"Federation**" means a federation of water users' associations established pursuant to this proclamation and wich is responsible for the administration and maintenance of a main irrigation and drainage system;

l/ "**Service provider**" means any public or private enterprise, other than federation , which conducts the management, operation and maintenance of the main irrigation and drainage system;

**m/ "Bureau**" means a regional water, Irrigation and Energy Development Bureau;

n/ **"Register of irrigation water users" association**" means the register required to be maintained by the bureau, pursuant to Article /36/ , sub article /1/ ,/d/ of this proclamation;

o/ "By –law'' means a by laws which shall be in effect, that has been approved with the general assembly and commencing from submitted and registered date to the bureau, after prepared with this proclamation and the organizational directives, to be issued by the bureau;

ፐ/ "ውስጠ-ደንብ" ማለት የማኅበሩ አባላት እና ልዩ ልዩ የሥራ ኃላፊዎች በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተሰጣቸውን የጋራ ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት እንዲችሉ በማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ፀድቆ በሥራ ላይ የሚውል የስነ-ስርዓት ደንብ ነው፤

ከ/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

2. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር የሴትንም ፆታ ያካትታል።

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት በጀትም ሆነ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ በክልሉ ውስጥ የተገነቡ ወይም ወደፊት በሚገነቡ የመስኖ መሠረተ ልማቶችና ህብረተሰቡ በሚጠቀምባቸው ባህላዊ የመስኖ መሠረተ ልማቶች ላይ የተደራጁ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራትን በሚመለከት ተፈፃሚ ይሆናል።

## 4. ዓላማዎች

አዋጁ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የመስኖና ድሬኔጅ አውታሮች በአግባቡ እንዲመሩ፣ እንዲተዳደሩ፣ ተገቢውን ጥገና በወቅቱ እንዲያገኙ እና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፤

p/ "Internal regulation" means a procedure regulation that shall be in effect approved with the general assembly of the association that members of the association and various officials enable to discharge the rendered communal responsibility properly, pursuant to the regulation of the association;

q/ "Person" means any natural or legal person.

2. Any expression in the masculine gender includes the feminine too.

## 3.Scope of Application

This proclamation shall be applicable to irrigation water users' associations on the constructed and to be constructed irrigation infrastructures and the traditional irrigation infrastructures, that the society serves in the region by the regional government budget as well as with the finance subsidy of the non-governmental organization.

## 4. Objectives

The proclamation shall have the following objectives:

1. Cause the irrigation and drainage systems in the region to be managed and administered properly, to get appropriate maintenance service timely and to be used;

2. የመስኖ እርሻ መሬትን እና የመስኖ ውሃን በአግባቡ በመንከባከብና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሥርዓት በመዘርጋት የመስኖ እርሻ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፤
3. በውኃ አጠቃቀም ዙሪያ በተጠቃሚዎች መካከል የሚነሱ ግጭቶችን በማስወገድ እና ተጠቃሚው እርስ በርሱም ሆነ ከሌሎች አጋር አካላት ጋር ተባብሮ የመስኖ ውሃን በአግባቡና በዘላቂነት መጠቀም የሚችልበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር።

## 5. ማኅበራት የሚመሩባቸው መሠረታዊ መርሆዎች

እያንዳንዱ ማኅበር በሚከተሉት መርሆዎች ላይ ተመስርቶ መቋቋምና መስራት አለበት ፣

1. ሚዛናዊ የውሳኔ አሠጣጥና ፍትሃዊ የመስኖ ውሃ ክፍፍል፤
2. የውሃ ብክነትንና ብክለትን፣ የአፈር መሸርሸርንና ጨዋማነትን የመከላከል፣ እንዲሁም የአካባቢ እንክብካቤንና ጥበቃን ለማጠናከር በአገልግሎት ክልል ውስጥ የሚገኘውን የመስኖና ድሬኔጅ አውታር መጠበቅና ማስተዳደር፤
3. በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ግልጽነትና አሳታፊነት ያለው የአሠራር ስርዓት መከተል፤
4. በውኃ አጠቃቀም ረገድ በአባላት መካከል ብሔርን፣ ፆታን፣ ሃይማኖትን ወይም በማናቸውም ሌሎች ተመሳሳይ ምክንያቶች ልዩነት አለማድረግ፤



2. Promote the irrigation farming product and productivity by properly handling and establishing the system of use of the irrigation farming land and the irrigation water;
3. Create a suitable condition to use the irrigation water appropriatey and sustainably that users themselves, as well as, collaborating with other stake holders and by resolving conflicts raised among users concerning to water usage.

## 5. Guiding Principles of Associations

Each association shall operate in accordance with the following guiding principles:

1. Fairness and equity in decision making and allocation of irrigation water;
2. Preventing wastage and pollution of water, combating erosion and salinity of soil and , protecting and administering irrigation and drainage system within the operation area so as to strengthen protection of the environment;
3. Applying transparency and participatory approach in decision making process;
4. Non–discrimination among members of an association in the utilization of water on the basis of ethnicity , gender, religion or any other similar grounds;

5. ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር በትብብር መስራት፤
6. ወጪን የመሸፈን እና ሀብት በቁጠባ የመጠቀም ስርዓትን መከተል፡፡

## 6. ስለ ማህበራት ተግባርና ኃላፊነት

የእያንዳንዱ ማኀበር ዝርዝር ተግባር በመተዳደሪያ ደንቡ የሚገለጽ ሆኖ ዓላማዎቹን እውን ለማድረግ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ዋና ዋና ተግባራት ማከናወን ይኖርበታል፡-

1. በአገልግሎት ክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የመስኖና የድሬኔጅ አውታሮች ያስተዳድራል፣ ይጠቀማል፣ ይጠግናል፣ እንዲሁም የውሃ ብክነትን ለመቀነስና የውኃ አጠቃቀምን ለመጨመር የሚያስችሉትን ዕቅዶች ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤
2. በመሬት ይዞታው ወይም ይኸው በሚያመርተው የሰብል ዓይነት ፍትሃዊ የመስኖ ውሃ ስርጭት እንዲኖር አስፈላጊውን መርሃ ግብር ያዘጋጃል፤
3. የመስኖ ውኃ አጠቃቀምን በተመለከተ በአባላት መካከል ለሚነሱ ክርክሮች በጋራ መግባባት እና በትብብር መንፈስ መፍትሄ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤
4. ዓመታዊ የሥራ ማስኬጃና የጥገና ወጪዎችን ለመሸፈን የሚያስፈልጉ መዋጮዎችን፣ የመስኖ ውኃ አገልግሎት ክፍያዎችን፣ የኢንቨስትመንት ወጪን ለመተካት የሚሰበሰቡ ክፍያዎችን እና በመተዳደሪያ ደንቡ የሚወሰኑ ሌሎች ክፍያዎችን ከአባላቱ ይሰበስባል፤

5. Work in collaboration with the pertinent stakeholders;
6. Complying with system of cost recovery and efficient use of resources.

## 6. Duty and Responsibility of the Associations

The detailed duty of each association being defined by the rule, shall perform the main activities indicated herein under to achieve its own objectives:

1. Administer, use and maintain the irrigation and drainage system in the service area, as well as and prepare plans that shall enabele to minimize the water wastage and increase water usage;
2. Prepare the necessary action plan to have equity irrigation water distribution on the land holding or produce the corn kind in same ;
3. Cause to resolve disputes raised among members with communal agreement and with the spirit of collaboration, concerning to the irrigation water usage and create a suitable condition in same ;
4. Collect, expenditures necessary to cover the annual work plan and maintenance, the irrigation water service payments , the to be collected payments to recover the investment expenditure and other payments that shall be determined by the rule, from members of the association;

5. የመስኖና ድሬኔጅ አውታሮችንና ሌሎች የመሠረተ ልማት አውታሮችን ጥገና ያካሂዳል፤
6. የአፈር መሸርሸርን፣ የውኃ ብክለትን፣ ጨዋማነትንና ጎርፍን መከላከል የሚቻልባቸውን እርምጃዎች ይወስዳል፣ የውኃ ቁጠባ አሰራርን ያስፋፋል፤
7. ንብረት ነክ መረጃዎችንና ሂሳቦችን በአግባቡ ይይዛል፣ ይጠብቃል፤
8. ከአባላቱ በኩል በሚያገኘው የጽሁፍ ስምምነት መሠረት አባላቱን በጋራ የሚመለከቱ ጉዳዮችን ይከታተላል፣ እንደአስፈላጊነቱ በፍርድ ቤት ክስ ይመሰርታል፣ ይከራከራል፤
9. የማኅበሩንና የአባላቱን ጥቅም ለማስጠበቅ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፤
10. ለመስኖ ልማቱ አስተዳደርና ጥገና ስራ የሚያስፈልጉትን ልዩ ልዩ መገልገያዎችና መሳሪያዎች በመግዛት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤
11. ዓላማዎቹን ለማሳካት ተገቢና አስፈላጊ ናቸው ተብለው የሚታመንባቸውን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል።

## 7. የአገልግሎት ክልል

1. እያንዳንዱ ማኅበር ተለይቶ የታወቀ የአገልግሎት ክልል ይኖረዋል፤

5. Conduct maintenance of the irrigation and drainage systems and other infrastructure systems;
6. Take measures that shall prevent soil erosion, water pollution, salinity and flooding; and shall expand the system of water saving activity;
7. Maintain and protect property related documents and accounts;
8. Incorporate issues concerning to members in common, pursuant to the written agreement in line with members; as deemed as necessary, sue and dispute in the court;
9. Work in collaboration with the pertinent bodies to preserve benefits of the association and members in same;
10. Procure various materials and equipments, necessary for irrigation development and maintenance activities, and properly utilize in same ;
11. Perform other related activities , that have been believed, appropriate and necessary to achieve its own objective .

## 7. Service Area

1. Each association shall have a defined service area;

2. የእያንዳንዱ ማኅበር የአገልግሎት ክልል የተለየና ራሱን የቻለ የመስኖ አውታር አሀዶችን ያቀፈ እና ማኅበሩ በሚያካሂደው የመስኖና ድሬኔጅ አውታር አማካኝነት ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ የውሃ አቅርቦት መገኛ ቦታዎች ሊኖሩት ይችላል፤
3. የአንድ ማኅበር የአገልግሎት ክልል ከሌላ ማኅበር የአገልግሎት ክልል ጋር መደራረብ የለበትም፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ ማኅበር አመሰራረትና ምዝገባ

### 8. ስለማኅበር አመሠራረት

አንድ ማኅበር፡-

1. ፍላጎቱ ባላቸው ሰዎች በፈቃደኝነት፤ ወይም
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ /11/ ንዑስ አንቀጽ /3/ፊደል ተራ ቁጥር (ሀ) መሠረት የመስኖ ውሃን ዘላቂ፣ ፍትሃዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም እና ለማስተዳደር እንዲቻል በቢሮው አማካኝነት ሊመሰረት ይችላል፡፡

### 9. ስለ ማኅበር ስያሜ

1. እያንዳንዱ ማኅበር ከሚሰራበት ቦታ መጠሪያ ጋር የተያያዘ ወይም ሌላ ስም ይኖረዋል፤
2. በየትኛውም ማኅበር ስም ውስጥ ***"የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበር ኃላፊነቱ የተወሰነ"*** የሚል ሀረግ መኖር አለበት፤
3. አንድ ማኅበር የተመዘገበበትን ስም ሌላ ማኅበር እንዳይጠቀም ተከልክሏል፤

2. The service area of each of each association shall comprise a distinct irrigation system units and may have a defined area of land that is through the irrigation and drainage system operated by that association from one or more water supply points;
3. The service area of an association may not overlap with another service area of an association.

## PART TWO

## Formation and Registration of Association

### 8. Formation of Association

**An association may be formed by:**

1. The will of interested persons ; or
2. The Bureau in accordance with Article/11/, sub article /3/ (a) of this proclamation, in order to utilize and administer irrigation water sustainably, equitably and efficiently.

### 9. Naming of Association

1. Every association shall have its own name attached to its area of operation or some other distinct name;
2. The phrase "irrigation water users'' association limited responsibility" shall be included in the name of every association;
3. No association shall use registered name of another association ;

4. የማንኛውም ማኅበር ስም በጉልህ ተጽፎ የማኅበሩ ሥራ በሚካሄድበት በማናቸውም ሥፍራ መለጠፍ አለበት፡፡ እንዲሁም በማኅበሩ ማስታወቂያዎች፣ ደብዳቤዎች፣ በማኅበሩ ስም በሚፈረም ሰነድ ላይ መፃፍ ወይም በማኅተም ተቀርጾ ማረፍ ይኖርበታል፤

5. ሁሉም ማኅበራት አንድ ዓይነት ምልክት ወይም አርማ ሊኖራቸው ይችላል።

## 10. በአባላት ፍላጎት ስለሚመሰረት ማኅበር እና የአመሠራረቱ ሥነ-ሥርዓት

1. አንድን ማኅበር፦

ሀ) የመሬት ይዞታ መብታቸውን መሠረት አድርገው ከባህላዊ የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ውሃ በሚያገኝ መሬት የሚጠቀሙ፤ ወይም

ለ) በመሬት የይዞታ መብታቸውና በዚህ አዋጅ መሠረት በቢሮው አማካኝነት ማኅበር እንዲመሰርቱ የተወሰነ ባይሆንም ከዘመናዊ የመስኖና ድሬኔጅ አውታሮች ውሃ በሚያገኝ መሬት የሚጠቀሙ ሰዎች በፍላጎት ሊመሰርቱት ይችላሉ፡፡

2. አንድ ማኅበር በአባላት ፍላጎት ሲቋቋም ከዚህ በታች የተመለከተውን ሥነ-ስርዓት ተከትሎ መፈፀም ይኖርበታል፦

4. The name of every, association shall be written boldly and be placed where the association conducts its activity. It shall also be written or stamped on every notice, letter, or document signed on behalf of the association;

5. All associations may have one type of symbol or emblem.

## 10 Formation of Association by the Initiation of Members and Formation Procedure

1. An association may be formed by the will of the following members:

a. Persons possessing land on the basis of landholding system and use such land with water supplied from a traditional irrigation and drainage system; or

b. Persons possessing land on the basis of landholding system and use such land with water supplied from a modern irrigation and drainage system in respect of which the Bureau not decided to establish an association pursuant to this proclamation.

2. Where an association , is formed with the initiation of its members, shall be performed following procedures stated herein under:

ሀ. የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች በፍላጎታቸው ማኅበር ሲመሰርቱ ቁጥራቸው ከአስራ አንድ የማያንስ መሆን አለበት፤ የማኅበሩን የአገልግሎት ክልል የሚለይ ጊዜያዊ አነሳሽ ቡድን መመስረት እንዲሁም ከአምስት የማያንሱ ወይም ከአሥራ ሁለት የማይበልጡ የማኅበር አባል ለመሆን የሚችሉ ሰዎች የሚይዝ የመሥራች ኮሚቴ ማደራጀት አለባቸው፤

ለ. የዚህ ንኡስ አንቀጽ ፊደል ተራ ቁጥር /ሀ/ድንጋጌ ቢኖርም ቢሮው ሁኔታዎች አስገዳጅ ሆነው በሚገኙበት ጊዜ የመስራች አባላት ቁጥር እስከ አምስት ዝቅ እንዲል ሊፈቅድ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፤

ሐ. ለታሰበው ማኅበር የተሟላ ውክልና እንዲኖር የመስራች ኮሚቴ አባላት ማኅበር ለመመስረት ከታሰበው የአገልግሎት ክልል ከሚገኙ ከተለያዩ አካባቢዎች የተውጣጡ ሰዎችን የሚያካትት መሆን አለበት፡፡

መ. መሥራች ኮሚቴው የራሱን ሊቀመንበር፣ ፀሐፊና ገንዘብ ያዥ በመምረጥ ከማኅበሩ ምሥረታ በፊት ለሚከናወኑ ተግባራት የሚያገለግል የራሱን የሥነ-ሥርዓት ደንብ ያዘጋጃል፤

3. መሥራች ኮሚቴው እንዲቋቋም ስለታሰበው ማኅበር ከቢሮው ጋር ምክክር በማድረግ የሚከተሉትን ሰነዶች ያዘጋጃል፡-

ሀ) እንዲቋቋም ለታሰበው ማኅበር ረቂቅ የመመሥረቻ ሰነድና መተዳደሪያ ደንብ፤

a. Where irrigation water users' form association with their initiation, their number shall not be less than eleven; to this effect they shall organize provisional initiative team to identify the service area of the proposed association and founders committee wihich shall not be less than five or not more than twelve potential members of the association;

b. Notwithstanding the provision of this sub article (a), it may allow the number of founder members to be minimized to five; particulars shall be determined with regulation to be issued for the implementation of this proclamation;

c. The founders committee shal be composed of persons representing different areas of the proposed service area so as to ensure fair representation of potential members of the proposed association;

d. The founders committee shall elect its chairperson, secretary and cashier and adopt its own rules of procedure to carry out activities preceding the formation of the association;

3. The founders committee, in consultation with the Bureau regarding the proposed association, shall prepare:

a) Draft memorandum and by laws of association;

ለ) ለታሰበው ማኅበር ረቂቅ በጀትና የሥራ መርሐ-ግብር ሰነድ፤

ሐ) እንዲቋቋም የታሰበውን ማኅበር የአገልግሎት ክልልና አሀዶች ካሉም የሚገኙበትን ቦታና መጠኑን የሚያሳይ ካርታ፤

መ) የታሰበውን ማኅበር ለመመስረት አባላት የሚያቀርቡትን ማመልከቻ ፤ እና

ሠ) የማኅበሩ አባላት ለመሆን የሚሹ ሰዎችን ስም፣ አድራሻ፣ ፊርማ የእያንዳንዱን አባል የመሬት ይዞታ መግለጫና ያላቸው ከሆነም የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ቁጥር።

4. መሥራች ኮሚቴው፡-

ሀ) እንዲቋቋም ለታሰበው ማኅበር አባል ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎችን ግንዛቤ የማሳደግ ሥራዎችን ያከናውናል፤

ለ)ሊመሰረት ለታሰበው ማኅበር አባላት ሊሆኑ ከሚችሉ አስቀድሞ በተወሰነው እና ስለአሰባሰቡ በቢሮው በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት የመመዝገቢያ ክፍያ ይሰበስባል፤

ሐ)ማኅበር ለመመስረት አባላት የሚያዘጋጁትን ማመልከቻ አቀናጅቶ እንዲፈረም ያደርጋል፤

መ) እንዲቋቋም በታሰበው ማኅበር ክልል ውስጥ የሚገኙ አሀዶች እንዲደራጁ ያደርጋል፡፡

b) A draft budget and work plan document of the proposed association;

c) A plan of the proposed service area that shows the size and location of the unis ,if any;

d) Application of the potential members for the formation of association; and

e) The lists of potential members of the proposed association, which shall incude the name , adress, signature and description of each potential member landholding and land certificate number.

4. The founders committee shall:

a) Perform awareness promotion activities for persons that shall be member to the proposed association;

b) Collect a registration fee, with pre-determined and pursuant to the rendered direction by the bureau, for collection of same to be members of the proposed association to be formed;

c) Integrate and cause to be signed the application that members shall prepare to form association;

d) Cause to be organized units in the service area of the proposed association;

5. መስራች ኮሚቴው ሊመሰረት የታሰበው ማኅበር አባላት ሊሆኑ ከሚችሉት ውስጥ ቢያንስ ግማሾቹ ማኅበሩን ለመመስረት በተዘጋጀው ማመልከቻ ላይ መፈረማቸው ከተረጋገጠ፡-

ሀ) የማኅበሩን ረቂቅ መመስረቻ ሰነድ፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ የበጀት እና የሥራ መርሐ-ግብር ተወያይቶ ለማጽደቅ፤ እና

ለ) ጊዜያዊ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላቱንም ሆነ ሌሎች የማኅበሩን ንዑሳን ኮሚቴዎች ለመምረጥ ይቻል ዘንድ የመሥራቾች ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ እንዲጠራ ያደርጋል፡፡

6. የታሰበው ማኅበር አባላት ከሚሆኑት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ የመሥራቾች ስብሰባ ምልአተ-ጉባኤ ይሆናል፡፡ የማኅበሩ መመስረትም ሆነ የመመስረቻ ሰነድና መተዳደሪያ ደንብ መጽደቅ በስብሰባው ላይ በተገኙት አባላት አብላጫ ድምጽ ይወሰናል፤

7. ጊዜያዊ የሥራ አመራር ኮሚቴው ማኅበሩን ለማስመዝገብ የሚከተሉትን የያዘ ማመልከቻ ለቢሮው ያቀርባል፡-

ሀ) የመሥራቾች ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ፤

ለ) በሦስት ቅጂዎች የተዘጋጀ የማኅበሩን መመስረቻ ሰነድ እና መተዳደሪያ ደንብ፤

ሐ) የታሰበው የአገልግሎት ክልል እና ካለም የአሀዶቹን አቀማመጥ የሚያሳይ ካርታ፤

መ) የታሰበውን ማኅበር ለመመስረት አባላት የፃፉት ማመልከቻ፤

ሠ) የበጀትና የሥራ መርሐ-ግብር ረቂቅ፤ እና

5. The founders committee shall convene founders meeting , when at least half of the potential members of the proposed association have signed the application for the formation of the association:

a) approve the draft memorandum and articles of association , budger and work –plan of the proposed association; and

b) cause to be announced the founders general assembly meetings to be able to elect the provisional management committee, as well as, sub –committees of the association.

6. There shall be a quorum of founders meeting where more than half of potential members of the proposed association are present at the meeting. The formation of the proposed association and decision on the approval of the memorandum and articles of association shall be passed by the majority vote of the members found at the meeting;

7. The provisional management committee shall submit an application for registration to Bureau together with:

a) The minutes of the founders meeting;

b) Three copies of memorandum and by laws of association;

c) The plan of the proposed service area and the location of the units , if any;

d) The application of the members for the formation of association;

e) The draft budget and work-plan; and

ረ) ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም በሚወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች የሚዘረዘሩ ሌሎች ሰነዶች፡፡

8. ቢሮው ማመልከቻውንና ተያይዘው የቀረቡትን ሰነዶች በ5 ቀናት ውስጥ በመመርመር ማኅበሩ ለምዝገባ የሚያበቃውን መስፈርት ያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ በመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበር መዝገብ ውስጥ በመመዝገብ ለማኅበሩ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

9. ቢሮው ማኅበሩ ለመመዝገብ ያቀረበውን ማመልከቻ ያልተቀበለው እንደሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያት በዝርዝር ለጊዜያዊ የሥራ አመራር ኮሚቴው በ5 ቀናት ውስጥ በፅሁፍ ያሳውቃል፡፡

## 11. በቢሮው ስለሚመሠረት ማኅበር እና የአመሰራረቱ ሥነ-ሥርዓት

1. ቢሮው ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በክልሉ መንግስት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በጀት በተገናቡ ወይም በሚገነቡ ዘመናዊ የመስኖና ድሬኔጅ አውታሮች ወይም ዘመናዊ የተደረጉ ባሕላዊ የመስኖና የድሬኔጅ አውታሮች የመስኖ ውሃ የሚጠቀሙ ማኅበራት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ ፊደል ተራ ቁጥር /ሀ/ መሠረት እንዲመሠረቱ ሊያደርግ ይችላል፤
2. ይህ አዋጅ ፀድቆ በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ የሚገነቡ የመስኖ አውታሮች ጥናታቸው ወይም ዲዛይናቸው ተጠናቆ ወደ ግንባታ ከመገባቱ በፊት ተጠቃሚዎች በማኅበር ተደራጅተው ግንባታውን መከታተል፣ ለግንባታው ተገቢውን ተሳትፎ ማድረግ እና ግንባታው እንደተጠናቀቀም ይህንኑ ከቢሮዉ ተረክበው ማስተዳደርና በዘላቂነት መጠቀም ይኖርባቸዋል፤

f) Other particulars that may be specified in regulations or directives to be issued for the implementation of this proclamation.

8. The bureau shall examine the documents within 5 days and if it is satisfied with the application and documents annexed thereto register an association in the register of irrigation water users' associations and issue a certificate of registration;

9. If the Bureau reject the application for the registration of an association, it shall give a written explanation to the provisional management committee within 5 days.

## 11. An Association Formed by the Bureau and Formation Procedure

1. The Bureau , after the entry into force of this proclamation, may make associations to be formed on the constructed or to be constructed by the regional government and non-governmental organizations budget , using irrigation water from a modern irrigation and drainage systems or traditional irrigation and drainage systems upgraded to modern irrigation and drainage systems pursuant to this Article, sub- article /3/ (a) of this proclamation;
2. After the approval and be in effect of this proclamation , prior to construction to be constructed irrigation systems study or designs finished, the users; organized in association shall follow up the construction, participate properly the construction and finishing of same administer and use sustainably by receiving same from the infrastructure entity;

3. አንድ ማኅበር በቢሮዉ አማካኝነት ሲቋቋም ቢሮው፡-
   ሀ) ስለሚመሠረተው ማኅበር አባላት ሊሆኑ ከሚችሉት ሰዎችና አግባብ ካላቸው አካላት ጋር ምክክር አድርጎ መግባባት ከተደረሰ በኋላ ማኅበር እንዲመሠረት ውሳኔ የሰጠ መሆኑን ያሳውቃል፤
   ለ) እንዲመሠረት ለወሰነው ማኅበር አባል ከሚሆኑት ሰዎች ጋር ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ውይይቶችን ያካሂዳል፣ የመስራች ኮሚቴውን ያስመርጣል፤
   ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ /10/ ንዑስ አንቀጽ /5/ የተመለከቱትን ረቂቅ ሠነዶች እንዲዘጋጁ በማድረግ መስራች ኮሚቴውን ይደግፋል፤
   መ) የታሰበውን ማኅበር ረቂቅ ሠነዶች የሚያፀድቅና ጊዜያዊ የሥራ አመራር ኮሚቴና ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎችን የሚመርጥ የመሥራቾች ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ የሚካሄድበትን ቀን ያሳውቃል።
4. ጊዜያዊ የሥራ አመራር ኮሚቴው በዚህ አዋጅ አንቀጽ /10/ ንዑስ አንቀጽ /7/ሥር የተመለከቱትን ሠነዶች ለምዝገባ ያቀርባል። አመዘጋገቡን በሚመለከት የዚህ አዋጅ አንቀጽ /10/ ንዑስ አንቀጽ /8/ እና /9/ ድንጋጌዎች በዚህ አንቀጽ መሠረት ለሚመሠረቱ ማህበራትም በተመሣሣይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

3. An association , established with regard to the Bureau, the Bureau:
   a) Shall notice that it rendered a decision the association shall be established in consultation with persons who shall be members and the appropriate bodies after achieving an agreement;
   b) Conduct discussions of awareness creation contineously with persons to be members of the proposed association, and cause to elect ther founders committee;
   c) Support the founders committee by preparing the indicated draft documents with sub –article /5/ of Article /10/ of this proclamation;
   d) Notify the date of meeting of the founders general assembly that shall approve the proposed association draft documents and elect provisional management committee and other sub-committees;
4. The provisional management committee shall submit the indicated documents to be registered under sub-article/7/ of article /10/ of this proclamation. Concerning to registration, Article /10/, sub-article/8/ and /9/ provisions of this proclamation shall also be similarly applicable to associations, that shall be established pursuant to this Article.

## 12. ስለ ሕጋዊ ሰውነት እና ኃላፊነት

1. በዚህ አዋጅ መሠረት ተመስርቶ የተመዘገበ ማኅበር ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ሕጋዊ ሰውነት ይኖረዋል፤
2. በዚህ አዋጅ መሠረት የተመሠረተ ማናቸውም ማኅበር ኃላፊነቱ የተወሰነ ሲሆን ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

## 13. ስለ ማኅበር መተዳደሪያ ደንቦች

1. የትኛውም ማኅበር የራሱ መተዳደሪያ ደንብ ይኖረዋል፤
2. የመተዳደሪያ ደንቡ ይዘት የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ) የማኅበሩን ስምና አድራሻ፤

ለ) የማኅበሩን ዓላማና ተግባር፤

ሐ) የማኅበሩን የአገልግሎት ክልል ፕላን ወይም ካርታ፤

መ) የማኅበሩ አባል ለመሆን የሚያበቁ መስፈርቶችን፤

ሠ) የማኅበሩን አባላት መብቶችና ግዴታዎች፤

ረ) የማኅበሩን አመራር አካላት ሥልጣን፣ ኃላፊነት እና ተግባር፤

ሰ)የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ የሚጠራባቸውን እና የሚመራባቸውን ሥነ-ስርዓቶች፤

ሸ) የማኅበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴና ሌሎች አካላትን ምርጫ፣ የሥራ ዘመንና ከኃላፊነት ስለሚታገዱበት ወይም ስለሚነሱባቸው ሁኔታዎች፤

ቀ) ክፍያዎች የሚወሰኑባቸውን ደንቦች፤

በ)የማኅበሩ ተግባራት የሚቋረጡባቸውን ሁኔታዎች::



## 12. Legal Personality and Liability

1. Any association formed and registered in accordance with this proclamation shall acquire legal personality as of the date of its registration;
2. Any association formed in accordance with this proclamation shall have limited liability and may not be held liable beyond its total assets.

## 13. By Laws of Association

1. Every association shall its own by-laws;
2. The content of the by-laws shall include the following particulars:
   a) The name and address of the association;
   b) The objective and activity of the association;
   c) The service area of the association supported by plan or map;
   d) Requirements for membership of the association;
   e) The rights and duties of the members of the association ;
   f) The powers, responsibilities and duties of the management bodies of the association;
   g) The procedure for calling and holding meetings of the general assembly of the association;
   h) Conditions for the election, term of office suspension and removal of elected officials of the management committee and other bodies of the association;
   i) Provisions on the setting of fees; and
   j) Conditions for the termination of the activities of the association.

3. የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ ሊሻሻል ይችላል፤ ሆኖም ማንኛውም የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ተግባራዊ የሚሆነው በቢሮው ፀድቆ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለ ማኅበር አባልነት እና ስለአባላት መብትና ግዴታ

### 14. ስለ ማኅበር አባልነት

1. በዚህ አዋጅ መሠረት በተቋቋመ በአንድ ማኅበር የአገልግሎት ክልል ውስጥ የሚገኝን መሬት አግባብ ባለው የመሬት ባለይዞታነት ሥርዓት ይዞ የሚጠቀም ማንኛውም ሰው የዚሁ ማኅበር አባል መሆን አለበት፤
2. በውርስ ወይም በሌላ በማናቸውም ሕጋዊ መንገድ በአንድ የአገልግሎት ክልል ውስጥ በሚገኝ መሬት የመጠቀም መብት ያገኘ ማንኛውም ሰው ቀደም ሲል የመሬቱ ተጠቃሚ የነበረው ሰው ለማኅበሩ አጠናቆ ያልከፈላቸውን መዋጮዎች እና ክፍያዎች በመክፈል የማኅበሩ አባል ይሆናል፤
3. ዕድሜው ለአካለ መጠን ያልደረሰ ወይም ዕድሜው ገፍቶ ወይም በአካል ጉዳት ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት በቀላሉ መንቀሳቀስና በማኅበሩ ሁለንተናዊ ተግባራት ላይ መሳተፍ የማይችል ማንኛውም የማኅበሩ አባል በህጋዊ አሳዳሪው /ሞግዚቱ ወይም በወኪሉ አማካኝነት መብትና ጥቅሞቹን ሊያስከብርም ሆነ ኃላፊነቶቹን ሊወጣ ይችላል፤

3. The by laws of an association may be amended by the special resolution of the general assembly ; provided, however, that any such amendment of the association shall be effective on the date of its approval and registration by the Bureau.

## PART THREE
## Membership of Association and Rights and Duties of Members

### 14. Membership of Association

1. Any person, who possess and uses land in accordance with the appropriate landholding system which is located within the service area of an association formed, pursuant to this proclamation, shall be a member of the association;
2. Any person, who acquires use right of the land located within the service area of an association by succession or any other legal method, shall become a member of that association upon payment of any outstanding contributions and fees due to the association from the previous user of that land that have not been collected;
3. Any person, who is incapable or elderly or disabled or by any other ground who can not move easily and participate on the overall activities of the association , cause to respect as well as discharge responsibilities with regard to tutor or delegator;

4. ከአንድ ማኅበር መቋቋም ጋር ተያይዘው የሚመነጩ መብቶችና ግዴታዎች በማኅበሩ የአገልግሎት ክልል ውስጥ ከሚገኙ ማሳዎች ጋር በቋሚነት የተያያዙና ማኅበሩ እስካልፈረሰ ወይም የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሻሻል ተከትሎ ማሳዎቹ ከማኅበሩ የአገልግሎት ክልል ውጭ እስካልሆኑ ድረስ ከማሳዎቹ ሳይነጠሉ የሚተላለፉ ናቸው፤
5. በማኅበሩ የአገልግሎት ክልል ውስጥ የሚገኝን መሬት ከሦስት ዓመት በላይ በኪራይ ውል የሚጠቀም ሰው የኪራዩ ዘመን እስከሚቋረጥበት ወይም እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ የማኅበሩ አባል እንደሆነ ይቆጠራል፤
6. በማኅበሩ የአገልግሎት ክልል ውስጥ የሚገኝ መሬት ሦስት እና ከሦስት ዓመት በታች ለሆነ ጊዜ በኪራይ ውል የሰጠ አከራይ የማኅበሩ አባል ሆኖ ይቆያል ፤ ሆኖም መሬቱን የተከራየው ሰው፦
   ሀ) የማኅበሩን ሕግጋትና ደንቦች የማክበር ግዴታ አለበት፤
   ለ) ከአከራዩ በሚሰጥ የጽሑፍ ፈቃድ በአከራዩ የማኅበርተኝነት መብቶች መገልገል ይችላል፡፡

## 15. የአባላት መብቶችና ግዴታዎች

1. ማንኛውም የማኅበር አባል በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፦
   ሀ) ማኅበሩ ከሚያከፋፍለው የመስኖ ውሃ ተገቢ ድርሻውን የማግኘት፤
   ለ) በማኅበሩ ከሚሰጠው ወይም በማኅበሩ በኩል ከሚገኙ ሌሎች አገልግሎቶች የመጠቀም፤

4. The rights and duties derive from the formation of an association are inseparable to the plots located within the service area of an association and shall be transferred with those plots while the association is existing or until such plots no longer lie within the service area following an amendment to the by laws of that association;
5. A person, who uses land located within the service area of an association on the basis of lease contract for more than three years, shall be considered as a member of the association until the termination or throughout the term of that lease;
6. A person , who leases his land possession located within the service area of an association for three and less than three years , shall continue as member of that association; provided, however that the lessee:
   a) Shall comply with the laws and regulations of the association;
   b) May exercise the membership rights of lessor in the association by written authorization of the latter.

## 15. Rights and Duties of Members

1. Any member of an association shall have the following rights, pursuant to this proclamation:
   a) to get a fair share of the irrigation water distributed by the association;
   b) to benefit from other services provided by, or through the association;

ሐ) የሚፈለግበትን ተገቢ የአገልግሎት ክፍያዎችን በማጠናቀቅ በማኅበሩ የተለያዩ የአመራር አካላት የመምረጥና የመመረጥ፤

መ) ለጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባዎች የመወያያ አጀንዳ የማስያዝ፤

ሠ) ለማኅበሩ ልዩ ልዩ አካላት የሚወዳደሩ እጩዎችን የመጠቆም፤

ረ) ማኅበሩ በቀጠረው ሠራተኛ ወይም ማኅበሩ በመሬቱ ላይ በሚያከናውናቸው የጥገና ሥራዎች ምክንያት ሆነ ተብሎ ወይም በቸልተኝነት በሰብሉ ወይም በመሬቱ ላይ ለደረሰ ጉዳት ከማኅበሩ ካሣ የማግኘት፤

ሰ) በሥራ ሰዓቶች የማኅበሩን ጽ/ቤት የመጎብኘት፣ የማኅበሩን መዛግብት የመመልከት፣ እንዲሁም በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት የማኅበሩን የሂሳብ አያያዝና የሥራ አመራር ዕቅዶችን የሚመለከት መረጃ የማግኘት፡፡

2. ማንኛውም የማኅበር አባል የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፦

ሀ) የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎችንና ውሳኔዎችን የማክበር፤

ለ) የማኅበሩን ልዩ ልዩ ክፍያዎች በወቅቱ የመፈፀም፤

ሐ)የመስኖ ውሃን ማኅበሩ በሚያወጣው የውሃ ክፍፍል መርሐ-ግብር መሠረት የመጠቀም፤

መ) በቸልተኝነት ወይም ሆነ ብሎ በማኅበሩ መሣሪያ ወይም መሠረተ-ልማት ላይ ያደረሰውን ጉዳት የመጠገን ወይም ለመተካት የሚያስፈልገውን ወጪ የመክፈል፤

c) To elect or to be elected for the different bodies of the association upon discharging fees of the association;

d) To propose agenda for discussion at general assembly meetings;

e) To propose candidates to the different bodies of the association for election ;

f) To receive compensation from the association for damages caused on his crops or land as a result of the international or negligent act of any employee of the association or as a result of the maintenance activities undertaken by the association;

g) To visit the office of the association during working hour, to peruse records of the association and to be provided, on request, with information regarding the association’s accounts, management plans.

2. Any member of an association shall have the following duties:

a) to respect the by –laws, directives and the decision of the association;

b) to pay fees timely of the association;

c) to use irrigation water in accordance with the association’s water distribution schedule;

d) to repair or to pay replacement costs of any equipment or infrastructure of the association damaged as a result of this intentional or negligent act;

ሠ) በማኅበሩ ሲጠየቅ ስለራሱ መሬትና ውሃ አጠቃቀም ተፈላጊ የሆነውን መረጃ የመስጠት፣

ረ) የማኅበሩ ሠራተኞች ወይም ከማኅበሩ ጋር የተዋዋሉ አገልግሎት ሰጪዎች የመስኖና የማፋሰሻ አውታሩን ለመሥራት ወይም ጥገና ሥራ ለማካሄድ እንደአስፈላጊነቱ መሣሪያዎችና ዕቃዎችን ሲያጉዙ ይዞታው ወደ ሆነው መሬት እንዲገቡ የመፍቀድ፣

ሰ) የመስኖና ድሬኔጅ አውታሮችን ከማጽዳትና ከመጠገን ጋር የተያያዙ ተግባራትን የማከናወን፣

ሸ) የመስኖና ድሬኔጅ አውታሩን አሠራርና ጥገና የሚመለከቱ ቴክኒካዊ ደንቦችን የማክበር፣ እና

ቀ) በማኅበሩ የሚሰጠውን ኃላፊነት በቅንነትና በታማኝነት የመወጣት፡፡

## 16. አባልነትን ስለማቋረጥ

1. በማኅበሩ የአገልግሎት ክልል ውስጥ በሚገኝ መሬት የመጠቀም መብቱን ያቆመ ማንኛውም አባል በመሬቱ የመጠቀም መብቱን ማቆሙን ለማኅበሩ በጽሑፍ በማሳወቅ ከአባልነቱ ሊወጣ ይችላል፣
2. ማንኛውም የማኅበር አባል ከማኅበሩ አባልነት እስከሚወጣበት ቀን ድረስ ላላጠናቀቀው ክፍያ በዕዳ ተጠያቂ ይሆናል፣
3. ማንኛውም የማህበሩ አባል ከማህበርተኝነቱ ሲሰናበት ምንም ዓይነት የሚጠይቀው አንዳች ክፍያ አይኖርም።

e) To provide relevant information, on request, to the association about his land and use of water;

f) To allow entrance of employees of the association, or service providers agreed with the association, to his land , with machines and equipments as necessary, in order to undertake operation and maintenance of the irrigation and drainage system;

g) To carry out activities related to cleaning and repairing of the irrigation and drainage systems;

h) To comply with applicable technical rules concerning the operation and maintenance of the irrigation and drainage system; and

i) To discharge with integrity and loyality that shall be provided responsibility with the association.

## 16. Termination of Membership

1. Any member, who has ceased his use right over the land located within the service area of an association, may terminate his membership, in writing , upon notifying the association;
2. Any member shall be liable for the outstanding fees due to the association at the date on which his membership terminates;
3. Any member of the association shall not have any payment when he dismissed from membership of the association .

## 17. ስለ ድምጽ አሠጣጥ

1. ማንኛውም አባል በአሀድ ወይም በጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባዎች ላይ አንድ ድምጽ ይኖረዋል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በማኅበሩ አባላት መካከል በያዙት መሬት ስፋት ወይም በሚጠቀሙት የውሃ መጠን ላይ ከፍተኛ የሆነ ልዩነት ካለ ቢሮው ከሚከተሉት በአንዱ ላይ ተመስርቶ የድምጽ ድልድል እንዲኖር ሊፈቅድ ይችላል፦
   ሀ) በአገልግሎት ክልል ውስጥ ካለው የማሳ ስፋት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ድምጽ እንዲኖረው በማድረግ፤ ወይም
   ለ) ለማኅበሩ ከከፈለው መዋጮ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ድምጽ እንዲኖረው በማድረግ፡፡
3. የድምጽ ድልድሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት እንዲሆን ከተፈቀደ እያንዳንዱ አባል ቢያንስ አንድ ድምጽ ይኖረዋል፡፡ ሆኖም ማንኛውም አባል በአንድ አሀድ ወይም በጠቅላላ ጉባኤ ከ20 ከመቶ በላይ የሆነ ድምጽ ሊኖረው አይችልም፡፡

## ክፍል አራት

## ስለአመራር አካላት

## 18. ስለማኅበሩ አመራር አካላት

1. የአንድ ማኅበር የአመራር አካላት፦
   ሀ) ጠቅላላ ጉባኤ፤
   ለ) የሥራ አመራር ኮሚቴ፤
   ሐ) የቁጥጥር ኮሚቴ፤ እና
   መ) የክርክር አወሳሰን ኮሚቴ፣ ናቸው፡፡

## 17. Voting

1. Any member shall have one vote in unit or at any meetings of the general assembly;
2. Notwithstanding the provision of sub article (1) of this Article, if there are significant difference in the sizes of the landholdings of members or the volume of water used , the Bureau may authorize the allocation of votes based on one of the following grounds:
   a) In proportion to the size plot of land within the service area; or
   b) In proportion to the amount of fees paid to the association.
3. In the event of allocation of vote pursuant to sub-article (2) of this Article, each member shall have a minimum of one vote; provided, however, that no member may hold more than 20 percent of total amount of votes in a unit or in the general assembly.

## PART FOUR

## Management Bodies

## 18. Management Bodies of an Association

1. the management bodies of an association shall be:
   a. The general assembly;
   b. The management committee;
   c. The control committee; and
   d. The dispute settlement committee.

2. አንድ ማኅበር በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ ሊፈቅድ ይችላል፤
3. የአንድ ማኅበር የአመራር አካላት ሥልጣንና ተግባር በዚህ አዋጅና በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ይሆናል፡፡

## 19. ስለ ጠቅላላ ጉባኤው

የጠቅላላ ጉባኤ አባላት የሆኑ በሙሉ በጠቅላላ ጉባኤዉ ስብሰባዎች ተገኝተዉ የመሳተፍ እና ድምፅ የመስጠት መብት አላቸዉ፡፡

## 20. የጠቅላላ ጉባኤው ሥልጣንና ተግባር

1. የማንኛውም ማኅበር ከፍተኛ የሥልጣን አካል የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ስር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ጠቅላላ ጉባኤው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
   ሀ) የማኅበሩን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት የማጽደቅ፤
   ለ) የማኅበሩን የሥራ አመራር አካላት፣ የቁጥጥር ኮሚቴ፣ የክርክር አወሳሰን ኮሚቴ እና ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎች አባላት የመምረጥ እና የመሻር፤
   ሐ) የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብና የውስጥ ደንብ የማጽደቅ እና የማሻሻል፤
   መ) በማኅበሩ አባላት የሚከፈል የመዋጮ እና የቅጣት መጠንን የመወሰን፤
   ሠ) የማኅበሩን ዓመታዊ ገቢና ወጪ መግለጫ እና የሀብትና ዕዳ መግለጫ እንዲሁም የሥራ አመራር አካላት ዓመታዊ ሪፖርት የማጽደቅ፤
   ረ)ማኅበሩን እንደገና የማደራጀት ወይም የማኅበሩን ሂሳብ ማጣራትን የሚመለከቱ ውሳኔዎችን የመስጠት፤



2. An association may provide in its by laws for the establishment of such other sub committees as may be necessary;
3. The powers and duties of the management bodies of an association shall be as determined by this proclamation and the association's by-laws.

## 19. The General Assembly

All general assembly members shall have a right to participate and render a decision by attending the general assembly meetings.

## 20. Powers and Duties of the General Assembly

1. The supreme organ of any association shall be the general assembly;
2. Without prejudice to the generality of provision specified under sub-article /1/ of this Article, the general assembly shall have the powers and duties to:
   a. Approve annual work plan and budget of the association;
   b. Elect and dismiss the members of the management body, the control committee, the dispute settlement committee and members of other sub committees;
   c. Approve or amend the by laws and internal regulations of the association;
   d. Set the amount of fees and fines payable by the members;
   e. Approve the annual income and expenditure statement and balance sheet and the annual report of the management bodies;
   f. Make decisions on the re-organization or liquidation of the association ;

ሰ) ማናቸውንም የማኅበሩን ንብረቶች መሸጥና በመያዣነት መስጠትን፣ ኢንቨስትመንትን፣ ብድር መበደርን ወይም ማኅበሩ ያለበትን ዕዳ ወይም እነዚህን የሚመለከቱ ገደቦችን የመወሰን፤

ሸ) በማኅበሩ ውስጠ-ደንብ መሠረት ከተወሰነ ዋጋ በላይ ያላቸውን ወይም ለማኅበሩ ከፍተኛ ፋይዳ ያላቸውን ውሎች የማጽደቅ፤

ቀ) በሥራ አመራር ኮሚቴ እና በሌሎች ኮሚቴዎች የሚቀርቡለትን ማናቸውንም ጉዳዮች መርምሮ የመወሰን፡፡

## 21. ስለ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎች

1. የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤
2. የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ምልዓተ-ጉባኤ በመተዳደሪያ ደንቡ ይወሰናል፡፡ ሆኖም ከ50+1 በታች ሊሆን አይችልም፤
3. የሥራ አመራር ኮሚቴው የማኅበሩ የቁጥጥር ኮሚቴ ወይም ከማኅበሩ አባላት አንድ ሦስተኛ የሚሆኑት በሚያቀርቡት የጽሁፍ ጥያቄ መሠረት የማኅበሩን አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ሊጠራ ይችላል፤
4. ስለጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ አጠራር፣ አጀንዳ አያያዝ፣ ተጨማሪ አጀንዳዎችን ስለማቅረብ እና አጀንዳዎቹ ለማኅበሩ አባላት የሚገለጹበት ሥነ-ሥርዓት በመተዳደሪያ ደንቡ ይወሰናል፤

g) set limitation on the sale and mortgaging or pledging of any assets owned by the association, investment or conclusion of loans, overdrafts or other financial liabilities of the association;

h) approve contracts above a certain value or of high significance to the association as may be specified in the by laws;

i) investigate and decide on any issue submitted to it by the management bodies or other committees.

## 21.Meetings of the General Assembly

1. The general assembly of an association that hold ordinary meeting at least once in a year;
2. The quorum of the general assembly shall be specified in the by laws of the association; however, it shall not be less than 50+1;
3. the management committee may call an extraordinary meeting of the general assembly upon written request of the control committee or one third of the members of the association;
4. The procedure for calling the meeting of the general assembly , setting agendas, proposing additional agendas and informing the agendas to their members shall be specified in the by laws;

5. የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባዎች የሚመሩት በሥራ አመራር ኮሚቴው ሊቀመንበር ወይም ሊቀመንበሩ በሌለበት ጊዜ በምክትል ሊቀመንበሩ ይሆናል፤

6. ማኅበሩን ለማፍረስ፣ ሂሳብ ለማጣራትና ዕዳን ለመክፈል ወይም ማኅበሩን እንደገና ለማደራጀት፣ መተዳደሪያ ደንቡን ለማሻሻል ወይም በመተዳደሪያ ደንቡ ሁለት ሦስተኛ ድምጽ እንዲሰጥባቸው በግልጽ ከተመለከቱት ጉዳዮች በስተቀር የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች በአብላጫ ድምጽ ያልፋሉ፤

7. የድምጽ አሠጣጡ ሥነ-ሥርዓት በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ መገለጽ አለበት፤

8. የጠቅላላ ጉባኤው ቃለ-ጉባኤ በሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ተፈርሞና በጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ የተገኙ አባላት ስም ዝርዝር እና ፊርማን የያዘ ሰነድ አባሪ ተደርጎ እና ማህተም ተደርጎበት መቀመጥ አለበት፡፡

## 22. ስለ ሥራ አመራር ኮሚቴ

1. እያንዳንዱ ማኅበር ቁጥራቸው ከአምስት ያላነሱ ወይም ከአስራ አንድ ያልበለጡ እና በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የሚመረጡ አባላትን የያዘና ለጠቅላላ ጉባኤ ተጠሪ የሆነ የሥራ አመራር ኮሚቴ ይኖረዋል፤

2. የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፤ ሆኖም በአንድ ወቅት የተመረጡ የኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን በአንድ ላይ እንዳያበቃ የሦስት ኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን ማብቂያ በፈረቃ እንዲሆን በመተዳደሪያ ደንቡ ይወሰናል፤

5. The meeting of the general assembly shal be presided by the chairperson or in his absence by the deputy chairperson of the management committee;

6. The decision of the general assembly shall be passed by a simple majority vote except in case of dissolution, liquidation or reorganization of the association or amendment to its by laws or any other matters directly specified in its by –laws to be decided by a two third majority vote;

7. The procedures for voting shall be described in the by laws;

8. The minutes of the general assembly shall be kept in the record of the association, signed by the management committee members and contain , as annex , the names and signatures of members of the association in attendance of the general assembly.

## 22. Management Committee

1. Every association shall have a management committee to be elected in accordance with the by laws of the association, which is accountable to the general assembly and whose members shall not exceed eleven and not be less than five;

2. The term of office of the management committee shall be five years; provided, however, that not to expire the terms of the committee members elected at the same time at once , the stagger for three of them shall be specified in the by laws of the association;

3. ማንኛውም የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል ከሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመን በላይ ሊመረጥ አይችልም፤
4. የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል የማኅበሩን የአገልግሎት ክልል ከላይኛው እስከ ታችኛው የመስኖ ልማት አካባቢዎችን እንዲወክል ወይም ዕጩዎች እንዲጠቆሙ ተደርጎ ከእነዚህ ከተወከሉ ወይም ከተጠቆሙ አባላት መካከል እንዲመረጥ ሊደነግግ ይችላል፤
5. አንድ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል በተመሣሣይ ጊዜ የቁጥጥር ኮሚቴ ወይም የክርክር አወሳሰን ኮሚቴ አባል ሆኖ ማገልገል አይችልም፤
6. ማንኛውም የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል የግል ፍላጎት ግጭት ሊያስከትል የሚችል ሁኔታ ሲከሰት ይህንኑ ማሳወቅና በሥራ አመራር ኮሚቴ ውይይቶችና ውሳኔዎች መሳተፉን ማቆም አለበት፤
7. የገንዘብ መቀጫዎችን ጨምሮ ያልተከፈለ የማኅበሩ ዕዳ ያለበት ወይም በተደጋጋሚ ለማኅበሩ መክፈል የሚገባውን ክፍያዎች በወቅቱ የማይከፍል ማንኛውም አባል ለሥራ አመራር ኮሚቴው አባልነት ምርጫ የመቅረብ መብት አይኖረውም፤
8. ለሥራ አመራር ኮሚቴ አባልነት የተመረጡ አባላት ከመካከላቸው ሊቀመንበር፣ ምክትል ሊቀመንበር፣ ፀሐፊ እና ገንዘብ ያዥ ይመርጣሉ፡፡

## 23. የሥራ አመራር ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር

የሥራ አመራር ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ሆኖ በተለይ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራትን ይጨምራል፡-



3. Any member of the management committee shall not be elected for more than two consecutive terms;
4. The by –laws of the association may provide that a member of the management committee shall be represented the irrigation water areas from low to high of the service area of the association or to be selected candidates elected among the representatives or the candidates;
5. A management committee member shall not serve as a control committee or a dispute settlement committee member at the same time;
6. Any member of the management committee shall declare and cease his participation in the discussions and decisions of the management committee when there is conflict of interest;
7. No member shall have the right to stand for election to the management committee when he is subject to outstanding liabilities including fines to the association or who shall not pay the appropriate fees timely and repeatedly to the association;
8. Those members elected for management committee shall elect chairperson, vice chairperson, secretary and treasurer from among themselves.

## 23. Powers and Duties of the Management Committee

The powers and duties of the management committee shall be specified in the by laws of the association and in particular shall include the following :

1. በጠቅላላ ጉባኤው የተወሰኑ ውሳኔዎችን የማስፈፀም፣
2. የማኅበሩን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት የማዘጋጀትና ሲፈቀድም ተግባራዊ የማድረግ፣
3. የጠቅላላ ጉባኤውን የስብሰባ አጀንዳ የማዘጋጀት፣
4. በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባ የመጥራት፣
5. የማኅበሩን ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ቃለ-ጉባኤዎችን በጽሁፍ የመያዝ፣
6. ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ እና የበጀት ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤው የማቅረብ፣
7. የማኅበሩን መዛግብትና ሂሳብ በሚገባ የመያዝ፣
8. በዚህ አዋጅ ወይም በመተዳደሪያ ደንቡ የተደነገጉ ወይም በጠቅላላ ጉባኤው የተወሰኑ ሌሎች ተግባራትን የመፈፀም፡፡

## 24. ስለሥራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባዎች

1. የሥራ አመራር ኮሚቴ በየወሩ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፣
2. የሥራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባ ምልዓተ-ጉባኤ በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ የተወሰነው ይሆናል፡፡ ሆኖም ከ50% ሲደመር አንድ በታች ሊሆን አይችልም፣
3. የሥራ አመራር ኮሚቴው ውሳኔዎች በስምምነት ያልፋሉ፣ ሆኖም ስምምነት ላይ መድረስ ያልተቻለ እንደሆነ በድምጽ ብልጫ መወሰን እንዲቻል መተዳደሪያ ደንቡ ሊፈቅድ ይችላል፣
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የሥራ አመራር ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፣

1. To implement decisions given by the general assembly ;
2. To prepare the annual work program and budget of the association and implement same upon approval;
3. To prepare agenda for the meeting of the general assembly;
4. To call the general assembly in accordance with the by-laws of the association;
5. To maintain the minutes of meetings of the general assembly in writing;
6. To submit report to the general assembly on the activity and budget of the association;
7. To maintain the documents and books of accounts of the association;
8. To implement such other activities specified in this proclamation or in the by laws or determined by the geneal assembly.

## 24.Meetings of the Management Committee

1. The management committee shall convene its ordinary meeting once in every month; provided, however , that it may hold extraordinary meetings at any time as may be necessary;
2. The quorum for the meeting of the management committee shall be as specified in the by laws of the association. Provided, however, not be less than 50 percent;
3. The decisions of the management committee shall be passed by consensus ; in case of lack of consensus, the by –laws may authorize the passing of decision by majority vote;
4. Without prejudice to the provisions of this Article, the management committee may adopt its own rules of procedure.

## 25. ስለሥራ አመራር ኮሚቴው ሊቀመንበር

1. የሥራ አመራር ኮሚቴው ሊቀመንበር የማኅበሩም ሊቀመንበር ነው፡፡
2. ሊቀመንበሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
   ሀ) የሥራ አመራር ኮሚቴውን ስብሰባ ይጠራል፣ የኮሚቴውንና የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባዎች ይመራል፤
   ለ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ማኅበሩን ይወክላል፤
   ሐ) በስራ አመራር ኮሚቴው ውሳኔዎች መሠረት ውሎችንና ሌሎች ሕጋዊ ሠነዶችን ይፈርማል፤
   መ) በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የተዘረዘሩትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡
3. ሊቀመንበሩ ተግባሩን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ የማኅበሩ ምክትል ሊቀመንበር እርሱን ተክቶ ይሠራል፡፡

## 26. ስለ ሥራ አመራር ኮሚቴ ፀሐፊ

የሥራ አመራር ኮሚቴው ፀሀፊ በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ከሚሰጠው በተጨማሪ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የማኅበሩን ጽ/ቤት ያደራጃል፤
2. የማኅበሩን ሠነዶች በአግባቡ ይይዛል፣ ይጠብቃል፤
3. የማኅበሩ ቃለ-ጉባኤ በሚገባ መያዙን ያረጋግጣል፤
4. የማኅበሩን የጽሕፈት ሥራዎች በኃላፊነት ይመራል፤
5. በሊቀመንበሩ እና በስራ አመራር ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 25. The Chairperson of the Management Committee

1. The chairperson of the management committee shall be the chairperson of the association;
2. The chairperson shall have the following powers and duties to:
   a) call for the management committee, and chair the meetings of the committee and the general assembly;
   b) represent the association in its dealings with third parties;
   c) sign contracts and other legal documents in accordance with resolutions of the management committee;
   d) undertake other duties specified in the by laws.
3. The vice chairperson of the association shall act in place of the chairperson where the latter is not in a position to discharge his duties.

## 26. Secretary of the Management Committee

The secretary of the management committee shall have the following powers and duties in addition to be rendered with the by laws of the association:

1. Organize the secretariat of the association;
2. Maintain and keep properly the documents of the association;
3. Ensure that the minutes of the association are properly kept;
4. Responsibly direct the secretarial activities of the association;
5. Perform other duties assigned to him by the Chairson and the management committee.

## 27. ስለ ቁጥጥር ኮሚቴ

1. እያንዳንዱ ማኅበር በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጡ ከሦስት ያላነሱ ወይም ከአምስት ያልበለጡ አባላትን የያዘ የቁጥጥር ኮሚቴ ይኖረዋል፤
2. የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፤
3. የቁጥጥር ኮሚቴ አባል ከሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመን በላይ ሊመረጥ አይችልም፤
4. በአንድ ወቅት የተመረጡ የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን በአንድ ላይ እንዳያበቃ የኮሚቴው አባላት የሥራ ዘመን ማብቂያ ጊዜ የተለያየ እንዲሆን በመተዳደሪያ ደንቡ ይወሰናል፤
5. አንድ የቁጥጥር ኮሚቴ አባል በተመሣሣይ ጊዜ የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም የክርክር አወሳሰን ኮሚቴ አባል ሆኖ ማገልገል አይችልም፤
6. የቁጥጥር ኮሚቴው ተጠሪነት ለጠቅላላ ጉባኤው ይሆናል፡፡

## 28. የቁጥጥር ኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር

የቁጥጥር ኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር በመተዳደሪያ ደንቡ የሚወሰን ሆኖ በተለይ የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባራት ይጨምራል፡-

1. የሥራ አመራር ኮሚቴው ኃላፊነቱን በትክክል መወጣቱን ይከታተላል፤
2. የማኅበሩ ገንዘብና ንብረት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

## 27. The Control Committee

1. Every association shall have a control committee composed of not less than three or not more than five members elected by the general assembly;
2. The term of office of the control committee shall be three years;
3. The member of control committee shall not be elected more than two consecutive term of office;
4. The terms of the members of the control committee shall be staggered in the by laws not to expire the terms of all members elected at one time ;
5. A member of the control committee may not at the same time serve as a member of the management or a dispute settlement committee;
6. The control committee shall be accountable to the general assembly.

## 28. Powers and Duties of the Control Committee

The powers and duties of the control committee shall be specified in the by laws of the association, and specially it shall include the following powers and duties of same :

1. To follow up that the management committee is discharging its responsibilities properly;
2. To supervise that the funds and property of the association are properly utilized;

3. የማኅበሩ የሂሳብ እና ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች በማኅበሩ መተዳደሪያ እና በውስጠ-ደንቡ መሠረት መከናወናቸውን ይከታተላል፣ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የኦዲት ምርመራ እንዲካሄድ ያደርጋል፤
4. ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርቱን አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል።

## 29. ሥለ አመራር አካላት የወል ድንጋጌዎች

1. የሥራ አመራር፣የቁጥጥር እና የክርክር አወሳሰን ኮሚቴዎች አባላት የማኅበሩ ተቀጣሪዎች ስላልሆኑ ደመወዝ አይከፈላቸውም፤ሆኖም ተግባራቸውን ሲያከናውኑ ያወጧቸው ተገቢነት ያላቸው ወጪዎችን በሚሸፍን መልኩ የማኅበሩን በጀት መሠረት አድርጎ በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ወይም ውስጠ-ደንብ በሚወሰነው መሰረት አበል ሊከፈላቸው ይችላል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፤
2. የሥራ አመራር፣የቁጥጥር ወይም የክርክር አወሳሰን ኮሚቴ አባል፡-
   ሀ. ተግባሩን መወጣት ካልቻለ፤
   ለ. በፕሮግራም በተያዙ ስብሰባዎች ላይ ያለበቂ ምክንያት ለሦስት ጊዜ ካልተገኘ፤ ወይም
   ሐ.ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በተከታታይ ከሦስት ጊዜ በላይ ለሆነ ጊዜ በኮሚቴ ስብሰባ ላይ መገኘት የማይችል ከሆነ፣በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ከኃላፊነት ሊነሳ ይችላል፡፡ዝርዝር አፈፃፀሙ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

3. To follow up that the financial and other activities of the association are undertaken in accordance with the by laws and internal regulation; and carry out audit at least once in a year;
4. To prepare and submit an annual audit report to the general assembly.

## 29. Common Provisions of the Management Bodies

1. The members of the management, the control and the dispute settlement committees are not entitled to receive salary as they may not be employees of the association; provided, however, that they may be entitled to reimbursement of reasonable expenses incurred during their functions and allowance in accordance with the budget of the association; pursuant to the decision of the by laws or internal regulation of the association; the particulars implementation shall be determined with directives to be issued for the execution of this proclamation;
2. A member of the management, control or dispute settlement committee may be removed from office pursuant to a decision of the general assembly on the grounds of:
   a. Failure to discharge his duty;
   b. Failure to attend scheduled meetings for three times ; or
   c. Not able to attend the meeting of the committee for more than three consecutive times on the grounds of force majeure , the member may be removed from his responsibility with the decision of the general assembly ; particulars implementation shall be determined with directives, that the Bureau shall issue.

3. የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ አንድን ተመራጭ ከኃላፊነቱ በሚያነሳበት ወቅት በምትኩ ሌላ መምረጥ አለበት፡፡

## 30. ስለማኅበሩ ሠራተኞች

1. ማንኛውም ማህበር የራሱን ሥራ አስኪያጅ፣ የቴክኒክ ወይም የጥገናና የአሰራር ክትትል ባለሙያ እና ሌሎች የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን ሊቀጥር ይችላል፤
2. ዝርዝሩ በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ሆኖ የማህበሩ ተቀጣሪ ሥራ አስኪያጅ በመስኖ ስራ አመራር ተስማሚ ሙያም ሆነ በቂ ልምድ ያለው እና የማኅበሩ አባል ያልሆነ ሰው መሆን ይኖርበታል፤
3. ሥራ አስኪያጁ ለሥራ አመራር ኮሚቴው ተጠሪ ሆኖ ምክር ይሰጣል፣ሲጠየቅም በስብሰባዎች ላይ ይገኛል፣ ሆኖም በውሳኔና በድምጽ አሠጣጥ ላይ አይሳተፍም፤
4. የሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር በመተዳደሪያ ደንቡ የሚወሰን መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ አመራር ኮሚቴው በተወሰነ የገንዘብ መጠን የተገደቡ አነስተኛ ውሎችን እንዲፈርም ሥልጣን ሊሰጠው ይችላል፤
5. የማኅበሩ ባለሙያዎችና የአስተዳደር ሠራተኞች ቅጥር ሁኔታ በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ወይም የውስጥ ደንብ ወይም በማኅበሩ የሠራተኞች አስተዳደር መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ ይገለፃል፤



3. The general assembly , in the event of removel of elected committee member, shall replace him by another member.

## 30. Employees of the Association

1. Any association may employ its own manager, the technic or the maintenance and the procedure follow up officer and other administrative supporting staff.
2. Subject to specific regulations to be issued in the by laws of the association, an employed manager of the associations, shall be a person with suitable qualification, as well as, relevant experiences of irrigation management and may not be member of that association;
3. The manager shall be accountable to the management committee and attend meetings when so requested , but may not participate in decision making and voting ;
4. Subject to specifc regulations to be issued in the by laws of the association, the management committee may authorize the manager to sign contracts of specific small amount of money;
5. The recruitment of officers and the administrative staff shall be conducted in accordance with the by laws or internal regulation or by the human resource administration directives of the adssociation. The implementation of particulars shall be defined by directives to be issued for the execution of the proclamation;

6. የአንድ ማኅበር ተቀጣሪ ሠራተኛ በተመሳሳይ ጊዜ የማኅበሩ ተመራጭ/የሥራ ኃላፊ ሆኖ ማገልገል አይችልም፡፡

## ክፍል አምስት
## ስለ ማህበራት ገቢ

### 31. ስለ ማኅበሩ የገቢ ምንጮች

1. የአንድ ማኅበር የገቢ ምንጮች፡-

ሀ.ከማኅበሩ አባላት የሚሰበሰብ የመመዝገቢያ ክፍያ፤

ለ. የማኅበሩ አባላት ዓመታዊ የጥገና እና የሥራ ማስኬጃ ክፍያ፤

ሐ. ስጦታ ወይም እርዳታ፤

መ. ለማኅበሩ ሳይከፈሉ ከዘገዩ ክፍያዎች ከሚገኝ ወለድ፤

ሠ. በባንክ ከሚቀመጥ ገንዘብ ወይም ከሌሎች ተመሳሳይ ምንጮች የሚገኝ ወለድ፤

ረ. ከአባላት መቀጫና ሌሎች ቅጣቶች የተሰበሰቡ ገቢዎች፤ እና

ሰ.ማኅበሩ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚከፈሉ ክፍያዎች ናቸው፡፡

2. እያንዳንዱ ማኅበር ለአስቸኳይ ጥገናዎች እና ማኅበሩ የሚገለገልበትን የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ለማሻሻል ወይም አድሶ በጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስፈልገውን ወጭ ለመሸፈን የሚውል የመጠባበቂያ ገንዘብ ማስቀመጥ ይኖርበታል፤

6. An employee of an association may not at the same time serve as an elected or official of that association.

## PART FIVE
## Income of Associations

### 31. Sources of Income of an Association

1. The sources of income of an association shall be:
   a. Registration fee collected from the members of the association;
   b. The annual maintenance and operational fee payable by members of the association;
   c. Gift or grant;
   d. Interest on outstanding fees due to the association;
   e. Interest on any money it deposited in Bank accounts or interest from other similar sources;
   f. The proceeds of fines or other sanctions imposed on members ; and
   g. Payments for services provided by the association .
2. Every association shall keep reserve fund for emergency repairs and for improvement or for the rejuvenation of the irrigation and drainage system;

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ስር የተመለከተው የመጠባበቂያ ገንዘብ ወጪ እስከሚደረግበት ጊዜ ድረስ ወለድ በሚያስገኝ የባንክ ሂሳብ ውስጥ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

32. ከአባላት ስለሚሰበሰብ የመመዝገቢያ ክፍያ

1. ሁሉም አባል የሚሆኑ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች አስቀድሞ በመተዳደሪያ ደንቡ በሚወሰነው መሠረት የመመዝገቢያ ክፍያ መክፈል አለባቸው፤

2. የመመዝገቢያ ክፍያ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ሊመሰረት ለታሰበው ማኅበር አባል ለመሆን ሲመዘገቡ አንድ ጊዜ ብቻ የሚከፍሉት ሲሆን የአባላትን የግል ፋይል ለማደራጀት፣ የማኅበሩን ጽ/ቤት ለመገንባትና በቁሳቁስ ለማደራጀት የሚውል ይሆናል፡፡

33. ስለ ዓመታዊ የአባላት የጥገና እና የሥራ ማስኬጃ ክፍያ

1. ማንኛውም ማኅበር ወጪዎችን ለመሸፈን አባሉ በአገልግሎት ክልል ውስጥ የያዘውን የማሳ ስፋት ወይም የሚያመርተውን የሰብል ዓይነት ወይም የሚጠቀመውን የመስኖ ውሀ መጠን መሠረት ያደረገ ዓመታዊ የጥገና እና የሥራ ማስኬጃ ክፍያ ማስከፈል አለበት፤

2. እያንዳንዱ አባል የሚከፍለው የጥገና እና የሥራ ማስኬጃ ክፍያ፡-

3. The reserve fund mentioned in sub – Article (2) of this Article, shall be kept in interest bearing bank account until such time as the fund is required.

32. **Registration Fee for Members**

1. All, who shall be members of the irrigation water users' shall pay a registration fee, pursuant to the decision of the by-laws in prior.

2. The registration fee, of the irrigation water users' to be member of the proposed association shall be payed at once , and it shall serve to organize individual profile of members , to build the association's office and organize with equipments.

33. **The Annual Maintenance and Operational Fee of the Members**

1. Every association shall collect from its members an annual maintenance and operational fee in proportion to the size of the plot of land or the type of crop produced or the amount of water use of member in the service area to cover its costs;

2. The amount of the maintenance and operational fee payable by each member shall be used to:

ሀ.የመስኖና ድሬኔጅ አውታሩን ለማካሄድ፣ለመጠገንና የውሃ መተላለፊያ ማንኛውም ቦይ ለማጽዳት የሚያስፈልገውን ወጪ ለመሸፈን፤

ለ. የመስኖና ድሬኔጅ አውታሩን ሥራ የማካሄድ ወይም የውሃውን መተላለፊያ መንገድ የመክፈት አገልግሎት ለሚሰጡ ሌሎች አገልግሎት ሰጭዎች የሚደረጉ ክፍያዎችን ለመሸፈን፤

ሐ. የማኅበሩን ሠራተኞች ደመወዝ እና ሌሎች ወጪዎች ለመሸፈን፤ እና

መ. ለማኅበሩ የመጠባበቂያ ገንዘብ ተቀማጭ ለማድረግ የሚውል ይሆናል፡፡

3. አነስተኛ የገንዘብ ወጪ ያለበት ማኅበር አባላት በስምምነት ዓመታዊ የአባላት መዋጮው ከፊል የጉልበት አስተዋጽኦን ጨምሮ በዓይነት እንዲሆን ማድረግ ይችላሉ፡፡

## 34. ስለ ውሃ አገልግሎት ክፍያ

አንድ ማኅበር እያንዳንዱ አባል ለመስኖ እርሻው በሚጠቀመው የውሃ መጠን ወይም በሚያለማው መስኖ መሬት መጠን ላይ የተመሰረተ የአገልግሎት ክፍያ እንዲፈጽም ማድረግ ይችላል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡



a. Cover the cost of operating and maintaining the irrigation and drainage system and the cost of cleaning any drainage ditches ;

b. Pay to the service providers for the operation of the irrigation and drainage system or the removal of obstructions from the irrigation canal ;

c. Pay salaries of staff and other costs of the association ;and

d. Maintain reserve fund for the association.

3. Members of an association which has small financial cost may agree to make some of the annual membership fee to be paid in kind including of labour.

## 34. **Water Delivery Charge**

An association may impose water delivery charge on each member in proportion to the volume of irrigation water used or by the size of the plot of the land of that member; implementation of the particulars shall be determined with regulation to be issued for the execution of this proclamation.

### 35. የኢንቨስትመንት ወጪን ለመመለስ ከአባላት ስለሚሰበሰብ ክፍያ

ማህበሩ ለዘመናዊ መስኖ ድሬኔጅ ግንባታ የወጣውን የኢንቨስትመንት ወጪ የአባላቱን የመክፈል አቅም ባገናዘበ ሁኔታ የሚጠቀሙትን ውሃ ወይም የሚያለሙትን የመስኖ መሬት መጠን መሰረት አድርጎ የተወሰነውን ክፍያ በመሰብሰብ ለቢሮዉ እንዲመለስ ያደርጋል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይገለፃል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ስለ ቢሮው ሀላፊነትና የቁጥጥር ስርዓት

### 36. ስለ ቢሮው ስልጣንና ተግባር

1. ቢሮው በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ልዩ ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

   ሀ. ከማኅበራት መቋቋምና ተግባራቸውን ከማከናወን ጋር በተያያዘ የግንዛቤ መፍጠሪያ ሥልጠና ይሰጣል፣

   ለ. የውሃ ሀብት አስተዳደርን፣ የሂሳብ አያያዝን፣የፋይናንስ ዕቅድ ማውጣትን፣የመስኖ ቴክኒኮችንና ልምዶችን፣ ጥገናንና ሥርዓተ-ፆታን ጨምሮ ለማህበራት የቴክኒክ ዕርዳታና ድጋፍ ያደርጋል፣

   ሐ. በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት አዳዲስ ማህበራት እንዲመሠረቱ ይደግፋል፣

   መ. የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት መዝገብን ያቋቁማል፣ ይይዛል፣

### 35. Charge of Members to Refund the Cost of Investment

Collect the determined charge and refund to the bureau, pursuant to the usage of water or the amount of irrigation land to be used with the consideration of members payment capacity of the association which discharges the investment cost applied for the modern irrigation and drainage construction.

## PART SIX

## Responsibility and Supervision Mechanism of the Bureau

### 36. Powers and Duties of the Bureau

1. The bureau shall have the following special powers and duties, pursuant to this proclamation to :

   a. Provide training and awareness creation in connection with the establishment and operation of associations;

   b. Provide technical assistance and support to associations including on issues of water management, accounting, financial planning, irrigation techniques and practices, maintenance and geneder issues;

   c. Support new associations to be formed in accordance with this proclamation;

   d. Establish and maintain the register of irrigation water users' associations;

ሠ. በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሠረት የሕግና የፋይናንስ ቁጥጥርና ምርመራ ያደርጋል።

2. ቢሮው የማኅበራትን የሕግና የፋይናንስ ቁጥጥርና ምርመራ ሲያካሂድ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና በሥራ የዋሉ መተዳደሪያና የሂሳብ አሠራር ደንቦችን ማክበራቸውን በማረጋገጥ ላይ የተወሰነ ይሆናል፤

3. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) የተመለከቱትን ሥልጣንና ተግባራት በሙሉ ወይም በከፊል አግባብ ላላቸው አካላት በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

e. Conduct the legal and financial supervision and investigation in accordance with the provisions this chapter.

2. The bureau, while exercising the legal and financial supervision and investigation of associations, shall be limited to the activities of the association whether it compiles with the provisions of this proclamation and applicable by law and accounting rules ;

3. The bureau may delegate some or all of its powers and duties specified in sub article /1/ of this Article to other appropriate bodies.

## 37. ስለ ዓመታዊ ሪፖርቶች

1. ማንኛውም ማኅበር የሩብ አመትና ዓመታዊ የሥራ፣የገቢና ወጪ ሪፖርቶችን በተፈቀደው የሪፖርት አቀራረብ ቅጽ መሠረት ለቢሮዉ ማቅረብ አለበት፤
2. ማንኛውም ማኅበር የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ30 ቀናት ውስጥ ዓመታዊ ሪፖርቱን ከሂሳብ መግለጫ ኮፒ ጋር በማያያዝ በተፈቀደው የሪፖርት አቀራረብ ቅጽ መሠረት ለቢሮው ማቅረብ አለበት፤
3. የማኅበሩ ዓመታዊ የሀብትና ዕዳም ሆነ የገቢና የወጪ መግለጫዎች ወይም የኦዲት ሪፖርቶች ለጠቅላላ ጉባኤው ቀርበው መፅደቅ አለባቸው፡፡

## 37. Annual Reports

1. Every association shall submit the quarter and annual work, income and expenditure reports to the bureau, in the approved format;
2. Every association shall, within 30 days, at the end of each budget year submit an annual report to the bureau , in the approved format, togerher with a copy of its accounts;
3. The annual assets, as well as, the liabilities, the income and expenditure statements or the audit reports of the association shall be submitted and approved by the general assembly.

## 38. ስለ ህግና ፋይናንስ ቁጥጥር

1. የማኅበሩን መዝገብ፡-

ሀ. የማኅበሩ አሰራር ትክክል ወይም ተገቢ አይደለም በማለት አንድ ሦስተኛው የማኅበሩ አባላት በጽሑፍ ሲጠይቁ፤ ወይም

ለ. የህግና የፋይናንስ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ተገቢነት የሌላቸው አሠራሮች ለመኖራቸው ከቁጥጥር ኮሚቴው ወይም ሌሎች አካላት ማስረጃ የተገኘ እንደሆነ፣ በቢሮዉ ሊመረመር ይችላል፡፡

2. ቢሮው የማኅበሩን መዛግብት መርምሮ አግባብ ያልሆነ የፋይናንስ አጠቃቀም ለመኖሩ ወይም ማኅበሩ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም በመተዳደሪያው እና በውስጠ-ደንቡ መሠረት እየሠራ አለመሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ካገኘ የሥራ አመራር ኮሚቴው የምርመራ ውጤቱን ለማኅበሩ አባላት የሚያቀርብበት አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ በ30 ቀናት ውስጥ እንዲጠራ ማዘዝ ይችላል፤

3. የሥራ አመራር ኮሚቴው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባ ሳይጠራ የቀረ እንደሆነ ቢሮው ራሱ የማኅበሩን አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ መጥራት ይችላል፤

## 38. Legal and Financial Supervision

1. The records of an association may be inspected by the bureau when:
   a. There is written request of two thirds of the members of that association alleging the incorrectness or impropriety of the function of the association; or
   b. There is primafacie evidence of legal or financial malpractice from the supervision committee or other bodies.
2. If the bureau having inspected the records of an association finds evidence of financial malpractice or non observance of the provisions of this proclamation or the by laws or internal regulation of the association, it may require the management committee to call an extraordinary meeting of the general assembly within 30 days to present the findings to the members;
3. If the management committee fails to call the meeting of the general assembly in accordance with sub article (2) of this Article, the bureau itself may call such extraordinary meeting

4. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የማኅበሩን ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ የጠራ እንደሆነ የአሰራር ችግሩን ለጠቅላላ ጉባኤው ሪፖርት በማድረግ የአሰራር ችግር ያስከተሉትን የሥራ አመራር አካላት አባላት ከኃላፊነት የሚነሱበትን እና አዲስ የሥራ አመራር አካላት አባላት የሚመረጡበትን ሁኔታ የማመቻቸት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

4. The bureau after having called the meeting in accordance with sub article ( 3) of this Article shall have the power to present the findings to the general assembly and to facilitate the removal of the management bodies of members involved in the malpractice and the election of new management bodies of members at the same time.

## 39. የቢሮውን ፈቃድ የሚሹ ጉዳዮች

1. ማንኛውም ማኅበር የሚከተሉትን ተግባራት ለማከናወን ከቢሮው በቅድሚያ የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት፦
   - ሀ.የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ ለማሻሻል፤.
   - ለ.የማኅበሩን የአገልግሎት ክልል ለማሻሻል፤
   - ሐ. ፌዴሬሽን ለመመስረት፤
   - መ.የማኅበሩን ንብረቶች በመያዣነት ለመስጠት ወይም ለማስያዝ፤
   - ሠ.የአንድን ማኅበር አባል የውኃ ተጠቃሚነት መብት እንዲሰረዝ ለማድረግ፡፡
2. ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከፊደል ተራ ቁጥር (ሀ) እስከ ፊደል ተራ ቁጥር (ሠ)መሠረት ለሚቀርብ የፈቃድ ጥያቄ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ በሚወሰን የጊዜ ገደብ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

## 39. Matters Requiring Authorization of the Bureau

1. Any association shall obtain prior written authorization of the bureau to conduct the following activities:
   a. to ammend the by-laws of an association;
   b. to modify the service area of an association;
   c. to form a federation;
   d. to pledge or mortgage assets of an association;
   e. to cancel the water use right of any member of the association.
2. The bureau shall, pass decision on the application submitted to it to obtain authorization in accordance with sub-article /1/ ,(a)-(e) of this Article , within the time limit determined by a regulation to be issued for the implementation of this proclamation.

## 40. ማህበራት መያዝ ስላለባቸው መዛግብት

ማንኛውም ማኅበር፡-

1. የአገልግሎት ክልሉን የሚያሳይ ካርታ፤
2. እንደአስፈላጊነቱ በየሦስት ወሩ የሚታደስ የአባላትን ዝርዝር እና የእያንዳንዱን አባል የመሬት ይዞታ ስፋት እና የሚገኝበትን ቦታ በዝርዝር የያዘ የአባላት መዝገብ፤
3. ማኅበሩ የሚቀበለውን ወይም የሚያወጣውን የውሃ መጠን የሚገልጽ መዝገብ፤
4. አባላት ያገኙትን የውሃ መጠን የሚያሳይ መዝገብ ወይም እያንዳንዱ አባል የመስኖ መሬቱን ለማጠጣት የፈጀበት ሰዓትና ለስንት ጊዜ እንዳጠጣ የሚያሳይ መዝገብ፤
5. አባላት ያሉባቸውንና የፈፀሟቸውን የመመዝገቢያ፣የጥገና፣ ሥራ ማስኬጃ፣የመስኖ ውሃ አገልግሎት እና ሌሎች ክፍያዎችን የሚያሳይ መዝገብ፤
6. የጠቅላላ ጉባኤና የሥራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባዎች ቃለ-ጉባኤዎችን የያዘ መዝገብ፤
7. የተፈፀሙ ግብይቶችንና ውሎችን የያዘ መዝገብ፤
8. የንብረት ቆጠራ የተደረገበት መዝገብ፤
9. ማኅበሩ በሚጠቀምበት የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ላይ የተደረጉ ቁጥጥሮችን፣ጥናቶችን እና ቅያሶችን የያዘ መዝገብ፤

## 40.Record to be kept by Associations

Any association shall maintain:

1. A plan showing the service area;
2. A register of members containing a description of the size and location of each member's landholding which shall be renewed and , as necessary , updated every three months;
3. a register of the volume of water received or discharged by the association;
4. a register of the volume of water received by members or a register which shows for how much hours each member water his own irrigation land; and for how much time , he waters in same;
5. A register of fees payed showing the registration, maintenance , operational the irrigation water service and others owned by members;
6. A register containing the minutes of the meeting of the general assembly and management committee;
7. A register containing performance marketing and contracts;
8. A register of an inventory of assets;
9. A register containing inspections, studies and surveys conducted on the irrigation and drainage system used by the association;

10. የተካሄዱ ጥገናዎችን የሚያሳይ መዝገብ፤
11. ትክክለኛና የተሟሉ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች፤ እና
12. በማኀበሩ ውስጠ-ደንብ የተዘረዘሩ ሌሎች መዝገቦች መያዝ አለበት፡፡

## 41. ቢሮው መያዝ ስላለበት መዝገብ

1. ቢሮው የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኀበራትን መዝገብ ያቋቁማል፣ይይዛል፤
2. ቢሮው የሚይዘው መዝገብ ስለእያንዳንዱ ማኀበር ቢያንስ የሚከተሉትን ዝርዝር መረጃዎች መያዝ አለበት፦
   ሀ. የማኀበሩን ስምና አድራሻ፤
   ለ. የእያንዳንዱ ማኀበር የምዝገባ ቁጥር እና የተመዘገበበትን ቀን፤
   ሐ. የአገልግሎት ክልሉን ስፋትና የሚገኝበትን ቦታ፤
   መ. የአባላቱን ቁጥር፤
   ሠ.የሥራ አመራር ኮሚቴውን አባላት፣ የሊቀመንበሩና የፀሐፊውን ሥም፣አድራሻና የስልክ ቁጥር፤
   ረ. ለማኀበሩ የተላለፈ የመንግስት መሠረተ ልማት ይዞታ ካለ ይህንኑ የሚያሳዩ ዝርዝር መረጃዎች።
3. የማኀበሩ አባላት በቢሮው ዘንድ የተቋቋመውን መዝገብ በማናቸውም መደበኛ የሥራ ሰዓት የማየት መብት ይኖራቸዋል፡፡

## 42. ስለ ድንበር ተሻጋሪ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት

1. የአንድ ማኀበር የአገልግሎት ክልል ሁለትና ከሁለት በላይ ዞኖችን የሚያካልል ሲሆን የማኀበሩን ምስረታና የሥራ ክንውን በሚመለከት ቢሮው ተቆጣጣሪ አካል ሆኖ ይሰራል፤

10. A record of maintenance activities;
11. Complete and accurate books of accounts and financial documents; and
12. Other records specified in the by laws of the association.

## 41.Register to be Kept by the Bureau

1. The bureau shall establish and maintain a register of irrigation water users' associations;
2. The register of the bureau shall contain at least the following details of each association:
   a. name and address of the association;
   b. the registration number and date of registration of each association;
   c. the size and location of the service area;
   d. the number of members;
   e. the name , address and telephone number of the management committee members, chairperson and secretary of the association;
   f. detailed evidences which shows the condition of government owned infrastructure transferred to the association, if any.
3. Members of the association shall have the right to see the register kept with the bureau at any time during office hours.

## 42.Trans-demarcation Irrigation Water Users Associations

1. In the event that the service area of an association crosses the boundaries of two or more zones, the bureau shall be the supervising body in respect of the formation and operation of such association;

2. የማኅበሩ የሥራ ክልል ሁለትና ከሁለት በላይ ወረዳዎችን የሚያካልል ሲሆን የማኅበሩን ምስረታና የሥራ ክንውን በሚመለከት ተቆጣጣሪው አካል አግባብ ያለው ዞን ውሀ፣ መስኖና ኢነርጅ ልማት መምሪያ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ስለማህበራት መፍረስ እና ሂሳብ ማጣራት

### 43. ስለማኅበራት መፍረስ

አንድ ማኅበር፡-

1. የመስኖና ድሬኔጅ አውታሩ አገልግሎት መስጠት የማይችልበት ሁኔታ ሲፈጠር፣
2. የተመሠረተበትን ዓላማ ለማሳካት የማይችል ሆኖ ሲገኝ፣
3. በማናቸውም ሌሎች ምክንያቶች የማኅበሩ ቀጣይነት የማያስፈልግ ሆኖ ሲገኝ የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በሁለት ሦስተኛ ድምጽ እንዲፈርስ ሲወስንና ይኸው ውሳኔ ለቢሮው ቀርቦ ሲፀድቅ ሊፈርስ ይችላል፡፡

### 44. የማኅበሩን ሂሳብ ስለማጣራት

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ/43/ መሠረት አንድ ማኅበር እንዲፈርስ ሲወሰን የሥራ አመራር ኮሚቴው ወይም ቢሮው ሂሳብ አጣሪ መመደብ አለበት፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተመደበ ሂሳብ አጣሪ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
   ሀ. የማኅበሩን መዛግብት፣ሰነዶችና ንብረት በመረከብ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ያደርጋል፣
   ለ. የማኅበሩን ሀብትና ንብረት ይሰበስባል፣

2. In the event that the service area of an association crosses the boundaries of two or more woredas, the appropriate supervision body shall be the zone water, irrigation and energy development in respect of the formation and operation of such association.

## PART SEVEN

## Dissolution of Association and Liquidation

### 43. Dissolution of Associations

An association shall be dissolved when:

1. the irrigation and drainage system no longer functional;
2. the purpose for which is formed can no longer be practically implemented ;or
3. its existene is no longer required for any other reasons; and , when the general assembly decides that the association to be dissolved, by a two thirds majority vote and upon approval of the bureau.

### 44. Liquidation of Association

1. When the dissolution of an association has been decided in accordance with Article /43/ of this proclamation, the management committee or the bureau shall assign liquidator;
2. A liquidator assigned pursuant to sub-article/1/ of this Article, shall have the following powers and duties:
   a. Receive records, documents and properties of the association and protect them from damage;
   b. Collect the assets and properties of the association;

ሐ. ከማኅበሩ ገንዘብ ጠያቂ የሆኑ ሰዎችን ይጠራል፤

መ. የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በወሰነው እና በቢሮው በፀደቀው ውሳኔ መሠረት የማኅበሩን ሀብትና ንብረት ያከፋፍላል፤

ሠ. የሂሳብ ማጣራቱን ሥራ በሚገባ ለማከናወን በሚያስፈልግ መጠን የማኅበሩን ሥራ ያንቀሳቅሳል፤

ረ. ማኅበሩን የሚመለከቱ ክርክሮችን ያካሂዳል፡፡

3. የማኅበሩ የመፍረስ ሂደት እስከሚጠናቀቅ ድረስ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች፣የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ-ደንብ በማኅበሩና በአባላቱ ላይ ተፈፃሚ መሆናቸው ይቀጥላል፤

4. የሂሳብ አጣሪው የአገልግሎት ዋጋ ከማኅበሩ ሂሳብ የሚከፈል ይሆናል፡፡

## 45. ማኅበርን ከመዝገብ ስለመሰረዝ

1. የሂሳብ ማጣራቱ ስራ እንደተጠናቀቀ ቢሮው ማኅበሩን ከመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት መዝገብ ይሰርዛል፤

2. ማኅበሩ ከመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት መዝገብ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ እንደፈረሰ ይቆጠራል፡፡

# ክፍል ስምንት

# ስለ ፌዴሬሽን

## 46. ስለፌዴሬሽን መመስረት

1. ዋናውን የመስኖና ድሬኔጅ አውታር በሙሉ ወይም በከፊል የሚያስተዳድር እና የመስኖ ውሃ ለተጠቃሚዎች የሚያቀርብ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት ፌዴሬሽን ሊመሰረት ይችላል፤



c. Call on creditors of the association;

d. Distribute the assets and properties of the association in accordance with the decision of the general assembly which is approved by the bureau;

e. Carry out necessary activities of the association for the proper liquidation of the affairs of the association;

f. Represent the association in legal proceedings.

3. Until the dissolution is concluded, the provisions of this proclamation and the relevant by –laws and internal regulation of the association shall continue to apply to the association and its members;

4. The remuneration of liquidator shall be paid from the accounts of the association.

## 45. Cancelation of Association from Register

1. Upon conclusion of the liquidation process, the bureau shall cancel the registration of the association from the register of irrigation water users' association ;

2. An association shall be considered dissolved from the date of its cancelation from the register of irrigation water users' association.`

# PART EIGHT

# Federation

## 46. Formation of Federation

1. To administer the whole or part of the main irrigation and drainage system and to supply irrigation water users; federation of irrigation water users' association may be formed;

2. የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ፌዴሬሽን በቢሮው ውሳኔ ወይም ፌዴሬሽኑ ያስተዳድረዋል ተብሎ ከሚጠበቀው ዋና የመስኖና ድሬኔጅ አውታር የመስኖ ውሃ ከሚጠቀሙ ማህበራት በአብላጫዎቹ ውሳኔ ሊመሠረት ይችላል፤

3. ከአንድ ዋና የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ውኃ ሊያገኙ የሚችሉ ማህበራት ሁሉ ዋናውን የመስኖና የድሬኔጅ አውታር የሚያስተዳድረው ፌዴሬሽን አባል መሆን አለባቸው፤

4. አንድ ፌዴሬሽን አባላት ከሆኑት ማህበራት በስተቀር ለሌላ ለማናቸውም አካል የመስኖ ውሃ አያቀርብም፣እንዲሁም በአባል ማኅበሩ በጽሑፍ ካልተፈቀደ በስተቀር በማኅበሩ የአገልግሎት ክልል ውስጥ ማናቸውንም ተግባር ማከናወን አይችልም፡፡

2. A federation may be formed by the decision of the bureau or by the decision of the majority of the association using irrigation water from the main irrigation and drainage system which could be managed by such federation;

3. Every association that can receive water from a main irrigation and drainage system managed by a federation shall be a member of that federation;

4. A federation may not supply irrigation water to anyone other than its member and undertake any activity within the service area of one of its members except by the written permission of that association.

**47. ስለፌዴሬሽን አሰያየም፣ስልጣን እና ተግባር**

1. ማንኛውም ፌዴሬሽን የሚያስተዳድርበትን ቦታ ስም ወይም ሌላ የተለየ መጠሪያ ቀጥሎ “የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ፌዴሬሽን” የሚል ቃላትን የያዘ የራሱ ልዩ ሥም ይኖረዋል፤

2. ፌዴሬሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ. ዋና ዋና የመስኖና ድሬኔጅ አውታሩን ማስተዳደር፣ሥራውን ማንቀሳቀስ፣ መጠገንና እንዳስፈላጊነቱም ለማሻሻል የሚያስፈልጉ ግንባታ ነክ ሥራዎችን ማካሄድ፤

**47. Naming, Powers and Duties of Federation**

1. Every federation shall have its own unique name which shall consist the name of the place where it manages or some other distinctive name followed by the words “federation of irrigation water users’ association.”

2. The federation shall have the following powers and duties:

   a. To manage, operate and maintain a main irrigation and drainage system and conduct construction works so as to upgrade;

ለ. የመስኖ ውሃ ፍጆታን የሚመለከቱ ውስጠ-ደንቦችን ማውጣትና ለአባል ማህበራት ለሰጠው አገልግሎት ክፍያዎችን መሰብሰብ፣

ሐ. አባላቱን በመወከል የመስኖ መሣሪያዎችን መግዛት፣መተካት፣ማንቀሳቀስና መጠገን፣

መ. አባላቱን በአቅም ግንባታ ስራዎች መደገፍ፡፡

3. ፌዴሬሽኑ በዚህ አዋጅ መሠረት የራሱ ሕጋዊ ሰውነት ይኖረዋል፣

4.በፌዴሬሽኑ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ እያንዳንዱ ማኅበር በማኅበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ውስጥ የሚሠሩ የተወሰነ ቁጥር ያላቸው አባላትን በመወከልና እነዚህ የኮሚቴ አባላትም የፌዴሬሽኑ ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ሆነው እንዲሰሩ ሊስማሙ ይችላሉ፣

5.በዚህ ክፍል የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለማኅበራት ተፈፃሚ የሚሆኑ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በፌዴሬሽኖችም ላይ ተፈፃሚዎች ይሆናሉ፡፡

## ክፍል ዘጠኝ
## ስለመስኖና ድሬኔጅ አውታሮች

### 48. ዘመናዊ የመስኖና ድሬኔጅ አውታሮችን ስለማስተላለፍ

1.አንድ ዘመናዊ የመስኖና ድሬኔጅ አውታር በክልሉ መንግስት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ወጪ ከተገነባ ወይም መልሶ ከታደሰ የዚህ መስኖና ድሬኔጅ አውታር ሙሉ ወይም የተወሰነ ክፍል በአንድ ማኅበር አገልግሎት ክልል ውስጥ የሚገኝ ወጪን የማስመለስ መርህን ተከትሎ ቢሮው ከማኅበሩ ጋር በሚደረሰው ስምምነት መሠረት በጥቅም ላይ የሚውልበትን መብት ለማኅበሩ ሊያስተላልፍ ይችላል፣



b. To issue internal regulations for irrigation water consumption and to collect fees from its member associations for the services provided to them;

c. To procure, substitute, operate and maintain irrigation equipments on behalf of its members;

d. To support its members in the capacity building activities.

3. A federation shall have legal personality, pursuant to this proclamation;

4. The members of a federation may agree in the by-laws of the federation that each association shall delegate a specified number of members of its management body to the federation which shall thereafter assume the functions of the general assembly;

5. Without prejudice to the provisions of this part, the provisions of this proclamation applicable to associations shall also apply to federations.

## PART NINE
## Irrigation and Drainage Systems

### 48. Transfer of Modern Irrigation and Drainage Systems

1. In agreement the bureau with the association based on the principle of cost recovery, transfer the use right of the whole or part of the modern irrigation and drainage system constructed or rehabilitated by the regional government and non- governmental association finance, if such irrigation and drainage system lies within the service area of an association;

2.አንድ ማኅበር በአገልግሎት ክልሉ ውስጥ በክልል መንግስት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ወጪ የተገነባ ወይም መልሶ የታደሰ ዘመናዊ የመስኖ ድሬኔጅ አውታር የተወሰነ ክፍል የተጠቃሚነት መብት ላልተወሰነ ጊዜ ተላልፎ እንዲሰጠው ለቢሮው ወይም ለተዋረድ አካሉ ማመልከት ይችላል፤

3.የውሃ አቅርቦት መገኛ ቦታ ግድብ፣የውሃ መጥለፊያ ውቅር፣የፓምፕ ጣቢያ ወይም ሌላ ዓይነት መሠረተ ልማት በአንድ ማኅበር የአገልግሎት ክልል ውስጥ የሚገኝ የሆነ እንደሆነ ውሃውን ከወንዝ፣ከጅረት፣ከማጠራቀሚያ፣ከኩሬ ወይም ከሌላ ተፈጥሯዊ መገኛ ለመውሰድ የሚያገለግለው መሠረተ-ልማት ለማኅበሩ አገልግሎት መስጠት እንዲችል ሊተላለፍ ይችላል፤

4.የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ማስተላለፊያ ስምምነት ሰነዱ በተወሰነ ቅጽ ሆኖ፡-

ሀ. የሚተላለፈው የመስኖና የድሬኔጅ አውታር ያለበትን ሁኔታ የሚያሳይ ዝርዝር መረጃ፤ እና

ለ. የመሠረተ ልማቱን ጥገና አስመልክቶ ስምምነት ያደረጉት ወገኖች ያሏቸውን መብቶችና ግዴታዎች፤ የሚያካትት መሆን አለበት፡፡

5.ቢሮው ለማህበራት ያልተላለፉና በራሱ ቁጥጥር ስር የሚገኙ የመስኖና ድሬኔጅ አውታር የተወሰኑ ክፍሎች ቢኖሩ በሚገባ ተጠብቀውና ተጠግነው መያዛቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።



2. An association may apply to the bureau or the subordinate body to transfer to itself, for indefinite period, part of a modern irrigation and drainage system constructed or rehabilitated by the regional government and non governmental organizations finance, if such infrastructure lies within its service area;

3. In the cases where the service area of an association lies in the water supply point of dam, weir , diversion structure, pump station or other type of infrastructure to which water is abstracted from a river , stream, reservoir, pond or other natural resource such infrastructure may also be transferred to the association;

4. The transfer agreement of irrigation and drainage system shall be in the form prescribed and contain:

a. Description of the condition of irrigation and drainage system to be transferred; and

b. The rightሰ and duties of the parties to the agreement in terms of the maintenance of the infrastructure.

5.The bureau, shall in any event ensure the protection and maintenance if there are parts of irrigation and drainage systems that are not transferred to any association and which remain under its control.

## 49. መረጃን ስለማስተላለፍና ስለቴክኒክ ቁጥጥር

1. አንድ ማኅበር ስለተላለፈለት የመስኖና የድሬኔጅ አውታር ጥገናና ስለሚገኝበት ሁኔታ ለቢሮው ወቅታዊ መረጃ መስጠት አለበት፤
2. በቢሮው አማካኝነት ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም ሠራተኛ ወደ አገልግሎት ክልሉ በመግባት ለማኅበሩ የተላለፈው የመስኖና የድሬኔጅ አውታር ያለበትን ሁኔታ ሊቆጣጠር ይችላል፤
3. በቢሮው የተወከለው ሠራተኛ ቁጥጥር ካደረገ በኋላ በተገኘው መረጃ መሠረት፡-
   ሀ. በመስኖና በድሬኔጅ አውታሩ ላይ ጉዳት ወይም ጥፋት እንዳይደርስ፤ ወይም
   ለ. በመስኖና ድሬኔጅ አውታሩ አጠቃቀም ምክንያት በመንግሥት ወይም በሦስተኛ ወገኖች ንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ፣ እንደጉዳዩ አስቸኳይነት የተወሰኑ ሥራዎች እንዲከናወኑ ማኅበሩን ሊያዝ ይችላል፡፡

## 50. ስለ ንብረት አገልግሎት

አንድ ማኅበር ለአባላቱ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የመስኖና ድሬኔጅ አውታሩን ለማደስ ወይም ለማልማት የአንድን መሬት አገልግሎት ማግኘት አስፈላጊ ሲሆን በቢሮው ተቀባይነት ሲያገኝ እና አግባብ ባለው ህግ መሠረት ለባለመሬቱ ካሳ አስቀድሞ ሲከፍል ይፈቀድለታል፡፡

## 49. Provision of Information and Technical Supervision

1. An association shall provide current information to the bureau concerning the maintenance and condition of transferred irrigation and drainage system;
2. A duly authorized officer of the bureau may enter into the service area of the association and inspect the condition of irrigation and drainage system transferred to it;
3. The authorized officer of the bureau, after having inspected the irrigation and drainage system, may require the association to undertake specified works where this is necessary as a matter of urgency:
   a. To prevent damage or harm on the irrigation and drainage system; or
   b. To prevent damage on government or third party property due to the usage of irrigation and drainage system;

## 50. Servitudes

An association, upon approval by the bureau and payment of compensation to the land possessor in accordance with appropriate law, shall be entitled to acquire servitude right over any one land necessary to rehabilitate or develop irrigation and drainage system for its members.

# ክፍል አስር
## ለማኅበራት ስለሚሰጡ አገልግሎቶች

### 51. ስለ አገልግሎት ሰጪዎች

1. አንድ ማኅበር ለአገልግሎት ክልሉ የሚውል ውሃ የሚያገኘው በፌዴሬሽን ከማይተዳደር የውሃ ማስተላለፊያ በር፣ የፓምፕ ጣቢያ ወይም በአንድ ዋና የመስኖና ድሬኔጅ አውታር ላይ ከሚገኝ ሌላ መሠረተ-ልማት ሲሆን፣ የመስኖ ውኃን ወይም ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለማኅበሩ የሚያቀርበው ዋና የመስኖ ድሬኔጅ አውታሩን ኦፕሬሽንና ጥገና የሚያካሂደው አገልግሎት ሰጪ ሊሆን ይችላል፤
2. መንግስታዊ አገልግሎት ሰጪዎች የሚቋቋሙበት ሁኔታ እና ለግል የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ፈቃድ የሚሰጥበት ሁኔታ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፤
3. አገልግሎት ሰጪው ለአንድ ማኅበር የመስኖ ውኃና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን የሚሰጠው ከማኅበሩ ጋር በሚደረገው የውል ስምምነት መሠረት ይሆናል፡፡

### 52. ስለ አገልግሎት አቅርቦት ስምምነት

1. ማንኛውም የአገልግሎት አቅርቦት ስምምነት የቆይታ ጊዜ ከአስር ዓመት ማነስ የለበትም፤ ሆኖም በአገልግሎት ተቀባይ ጥያቄ መሠረት ከአምስት ዓመት የማያንስ ነገር ግን ከአስር ዓመት በታች ለሆነ ጊዜ መስማማት ይቻላል፤

# PART TEN
## Provision od Services to Associations

### 51. Service Providers

1. In the cases Where the Water supply point of the service area of an association is a gate, turn out, pumping station or other infrastructure on the main irrigation and drainage system that is not managed by a federation, the irrigation water and other related services shall be provided to an association by a service provider responsible for the operation and maintenance of the main irrigation and drainage system;
2. The conditions for the establishmen of public enterprises or licensing private entities to provide the service shall be specified by regulation to be issued for the implementation of this proclamation;
3. A service provider shall provide irrigation water and other related services to an association on the basis of contract service agreement reached with the association.

### 52. Service Agreement

1. The term of every service agreement shall not be less than ten years; provided, however, that by the request of the association it could be less than ten years, but in no case it shall be less than five years;

2. ማንኛውም የአገልግሎት ስምምነት ወጥነት ያለው ሆኖ በተለይ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፦

ሀ. የውሃ መገኛውን ቦታ መረጃ፤

ለ. በዓመት የመስኖ ውኃ አገልግሎት የሚሰጥበት ወቅት፤

ሐ. በመስኖ ወቅት ውሃ ለማግኘት የሚቀርብ የጥያቄ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት፤

መ. አገልግሎት ሰጪው ውኃ በሚያቀርብበት ሁኔታ ላይ በሌሎች አግባብ ባላቸው አካላት የሚደረግበት ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ በየወሩ በሚወጣው መርሐግብር መሠረት ማኅበሩ በእያንዳንዱ የመስኖ ወቅት የሚያስፈልገውን ከፍተኛ የውሃ መጠን፤

ሠ. የውሃ ብክነትን፣ ብክለትንና ጨዋማነትን ለመቀነስ የሚወሰዱ እርምጃዎች፤

ረ. የውኃ አገልግሎት ክፍያን እና የአከፋፈሉን ሁኔታ፤

ሰ. ኃላፊነትንና በውኃ አጠቃቀም ላይ የተጣሉ ገደቦችን፤

ሸ. የውል ግዴታዎችን ባለመፈፀም የሚወሰኑ ቅጣቶችን፤ እና

ቀ. ውጤታማ የውኃ አጠቃቀምን ተግባራዊ ለማድረግ ወይም ውሃ ማቅረብን አስመልክቶ በአገልግሎት አቅራቢው የውሃ ማቅረብ ፈቃድ ውስጥ የተመለከቱ ሌሎች ግዴታዎችን ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች።

2. Any service agreement shall be made in a standard format and include, in particular, the following:

a. Information of the water supply point;

b. Season of the year in which irrigation water is to be supplied;

c. The procedure for requesting water supply during the irrigation season;

d. The maximum volume of water the association require during each irrigation season in accordance with a monthly schedule, subject to any restriction on the service provider to supply such water by any appropriate body;

e. Measures to be taken to reduce water wastage, pollution and salinity;

f. Charges and payment conditions;

g. Liabilities and limitations on the use of water;

h. Penalties for non compliance with the conditions of the contract; and

i. Other conditions necessary to promote the effective use of water or to implement any legal obligations of the service provider concerning the provision of water as stipulated in the water provision includes.

## 53. ስለ አገልግሎት ውሎች መሻሻል

1. የአገልግሎት ውሎች የሚሻሻሉት ወይም የሚለወጡት በሁለቱ ወገኖች ስምምነት መሠረት ይሆናል፤
2. በአገልግሎት አቅርቦት ስምምነቱ መሠረት አገልግሎት ሰጪው የውሃ እና ሌሎች አገልግሎቶችን አግዶ ሊያቆይ የሚችለው ማኅበሩ ያለበትን ክፍያ ከ120 ቀናት በላይ ሳይፈጽም የዘገየ እንደሆነ ብቻ ነው፤
3. በዚህ አዋጅ መሠረት የተፈፀመ የአገልግሎት ስምምነት ሊሰረዝ የሚችለው፡-
   ሀ. ከሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል አንዱ ስምምነቱን በተደጋጋሚ ባለማክበሩ በፍርድ ቤት የተወሰነ፤ ወይም
   ለ. ማኅበሩ የፈረሰ እንደሆነ ነው፡፡

## 54. የአገልግሎት ሰጪው ኃላፊነት

1. አንድ አገልግሎት ሰጪ በአገልግሎት ስምምነቱ መሠረት የውሃ መጠን ባለማቅረቡ ወይም በስምምነቱ የጊዜ መርሐ-ግብር መሠረት ውሃ ባለማቅረቡ በማኅበሩ ላይ ለደረሰበት ጉዳት ተመጣጣኝ ካሳ የመክፈል ኃላፊነት ይኖርበታል፤
2. አገልግሎት ሰጪው ለማኅበሩ የመስኖ ውሃ ለማቅረብ ካለመቻሉ የተነሳ ኪሳራ የደረሰበት ማንኛውም የማኅበሩ አባል ከአገልግሎት ሰጪው ላይ ካሳ ለመጠየቅ የሚሰላውን ካሳ መጠን ለማስላት እንደ አንድ የውሉ ተካፋይ ሆኖ ይቆጠራል፤



## 53. Variation of Service Agreement

1. The service agreement may be varied or amended by the agreement of both parties;
2. A service provider may suspend the supply of water and other services under a service agreement only if the association delays payment of any outstanding charges for more than 120 days;
3. A service agreement concluded in accordance with this proclamation may be terminated:
   a. by the decision of the court when one of the parties persistently fail to comply with the terms of the agreement; or
   b. on the dissolution of the association.

## 54. Liablity of the Service Provider

1. A service provider shall be liable to any compensation equitable to the damage the association sustained due to this failure to supply water in the agreed quantity or in accordance with the time schedule;
2. Any member of an association whe has sustained losses as a result of the inability of the service provider to provide irrigation water to the association shall be deemed to be a party to the contract for the purpose of calculating the amount of compensation to be claimed from the service provider;

3.አገልግሎት አቅራቢው የመስኖ ውሃውን ለማቅረብ ያልቻለው በሃገሪቱ የፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ/1792/ መሰረት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የሆነ እንደሆነ ለተጎጂው ካሳ አይከፍልም፡፡

3.Compensation may not be payable in case of the failure of service provider of the irrigation water with force majeure as defined in the civil code , Article/1792/ of the country.

## 55.ስለ ውሃ አቅርቦት ክፍያ አወሳሰን

## 55. Setting of Water Delivery Payment

1.አንድ ማኅበር ለአንድ አገልግሎት ሰጪ የሚከፍለው የውሃ አቅርቦት ዋጋ መጠን በቢሮው ይወሰናል፤

2.ቢሮው አንድ ማኅበር ለአገልግሎት ሰጪ የሚከፍለውን የውሃ አቅርቦት ዋጋ መጠን የሚወስነው፡-

ሀ. የማኅበሩ አባላት ለአስፈላጊ ጥገና ማስቀመጥ ያለባቸውን ገንዘብ፤

ለ. የማኅበሩ አባላት ለመስኖ ውሃ አቅርቦት ለመክፈል ያላቸውን አቅም፤ እና

ሐ. አገልግሎት ሰጪው ለኢንቨስትመንት ካዋለው ገንዘብ ጋር የተመጣጠነ ጥቅም የሚገኝበትን ሁኔታ በማመዛዘን ይሆናል፡፡

1. The amount of payment payable by an association to a service provider for the delivery of water shall be determined by the bureau;
2. In determining the amount of payment payable to the service provider, the bureau shall take into account:

a. the necessary reserve fund to be deposited for maintenance by the members of the association;

b. the ability of the members of the association to pay for irrigation water; and

c. the service provider's reasonable benefit of investment.

## ክፍል አስራ አንድ
## ስለክርክር አወሳሰን

## PART ELEVEN
## Dispute Settlement

## 56.ስለክርክር አወሳሰን ኮሚቴ

1. እያንዳንዱ ማኅበር በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጡ መልካም ስም ያላቸው እና የማያዳሉ ከሦስት የማያንሱና ከአምስት የማይበልጡ አባላት ያሉበት የክርክር አወሳሰን ኮሚቴ ይኖረዋል፤
2. የክርክር አወሳሰን ኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፤የኮሚቴው አባላት በተከታታይ ከሁለት የሥራ ዘመን በላይ ሊመረጡ አይችሉም፤

## 56. Dispute Settlement Committee

1. Every association shall have a dispute settlement committee elected by the general assembly consisting of not less than three and not more than five persons of high reputation and impartiality;
2. The term of office of a dispute settlement committee shall be five years; no member of such committee may be elected for more than two consecutive terms;

3.ለክርክር አወሳሰን በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ አባላት ከመካከላቸው አንዱን አባል የኮሚቴው ሊቀመንበር አድርገው ይመርጣሉ፤

4.አንድ የክርክር አወሳሰን ኮሚቴ አባል በተመሳሳይ ጊዜ የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም የቁጥጥር ኮሚቴ አባል ሆኖ ማገልገል አይችልም፡፡

**57.የክርክር አወሳሰን ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር**

1. የክርክር አወሳሰን ኮሚቴ፡-

ሀ. በውሃ አጠቃቀም እና ድልድል ምክንያት በማኅበሩ አባላት መካከል የሚነሱ ክርክሮችን፤

ለ. መተዳደሪያ ወይም የውስጥ ደንቦች በመጣሳቸው ምክንያት የሚቀርቡ አቤቱታዎችን፤

ሐ. የውሃ ክፍፍል መርሀ-ግብር አለማክበርን፤ እና

መ. በሥራ አመራር ኮሚቴ በሚሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ ይግባኞችን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ሰምቶ ውሳኔ የመስጠት ስልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

2. የክርክር አወሳሰን ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከፊደል ተራ ቁጥር (ሀ) እስከ ፊደል ተራ ቁጥር (ሐ) ከተመለከቱት ምክንያቶች በአንዱ አቤቱታ በጽሁፍ ወይም በቃል ሲቀርብለት፡-

ሀ.መጀመሪያ የክርክሩን ምንጭ በሊቀመንበሩ አማካኝነት በአስቸኳይ ያጣራል፤

3.Members of a dispute settlement committee elected by the general assembly shall elect one of them to be the chairperson of the committee;

4.A member of the dispute settlement committee may not at the same time serve as a member of the management committee or the comtrol committee.

**57.Powers and Duties of the Dispute Settlement Committee**

1. A dispute settlement committee shall have the powers and duties to hear and determine:

a. Disputes on water use and distribution between members of the association;

b. Disagreements related to the violation of the association's by –laws, or internal regulations;

c. Matters related to non observance of watering schedule; and

d. Appeals lodged against the administrative decisions of the management committee.

2. Upon receiving written or oral complaint on the grounds specified under paragraphs (a) to (c) of sub –article /1/ of this Article, the dispute settlement committee shall:

a. Promptly inspect the source of the problem by the chairperson;

ለ. አቤቱታው የቀረበው በጽሁፍ እንደሆነ ለተከሰሰው ሰው እንዲደርሰው እና በቀጠሮ ቀን መልስ ይዞ ቀርቦ እንዲከራከር መጥሪያ ይልካል፤

ሐ. የኮሚቴው ሊቀመንበር በሁለት ቀናት ውስጥ ጉዳዩን ለማየት ለክርክር አወሳሰን ኮሚቴ አባላት ይመራዋል፤

መ. በተያዘው የቀጠሮ ቀን ሁለቱንም ተከራካሪ ወገኖች ይሰማል፣የጽሁፍ ማስረጃዎቻቸውን ይመረምራል፣ አስፈላጊ ሲሆን የክርክሩ መነሻ የሆነው ቦታ ድረስ በመሄድ ጉዳዩን ያጣራል፤

ሠ. ከሁለት ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ በመስጠት ለተከራካሪ ወገኖች ያሳውቃል፡፡

b. Where the allegation is lodged in writing, issue summon on the respondents so as to respond on the complaint and avail himself for the hearing;

c. the chairperson of the dispute settlement committee shall refer to the members of the committee to hear the issue within two days;

d. hear both parties, examine their documentary evidence or may undertake site inspection, if necessary;

e. decide and announce its decision to the parties not more than two days.

## 58. አፈፃፀም

በዚህ አዋጅ መሰረት የተሰጠ ማናቸውም ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ በመደበኛ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ችሎት እንደተሰጠ ውሳኔ ተቆጥሮ በይግባኝ እስካልተሻረ ድረስ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

## 58. Execution

Any decision or order made in accordance with this proclamation shall be considered as the decision of regular civil bench of the court and shall be executed unless reserved by appeal.

## 59. ስለ ይግባኝ

በክርክር አወሳሰን ኮሚቴ ታይቶ በተሰጠ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ወገን ውሳኔው በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ማኅበሩ ለሚገኝበት ወረዳ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

## 59. Appeal

Any party dissatisfied with the decision of dispute settlement committee may lodge appeal to the woreda court, which the association is found within 30 days, after the decision is rendered.

# ክፍል አስራ ሁለት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 60.አስተዳደራዊ ቅጣቶች

1. አንድ አባል፡-

ሀ. የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ያፀደቀውን መተዳደሪያ ደንብ ወይም ማናቸውንም ውስጠ-ደንብ ያላከበረ እንደሆነ፤

ለ. በመተዳደሪያ ደንቡና በዚህ አዋጅ መሠረት የተወሰኑትን ክፍያዎች በወቅቱ ያልከፈለ እንደሆነ ወይም በሚያስፈልግ ጊዜ የጉልበት ሥራ አስተዋጽኦ ያላደረገ እንደሆነ፤

ሐ. የመስኖ ውሃን ማኅበሩ ባወጣው መርሐ-ግብር መሠረት የማይጠቀም ከሆነ፤

መ. ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት በማንኛውም የማኅበሩ ንብረት ወይም መሣሪያ ላይ ላደረሰው ጉዳት የማስጠገኛ ወይም የመተኪያ ወጪ ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ፤

ሠ. ስለመሬቱ ወይም ስለውሃ አጠቃቀሙ ለማኅበሩ ተገቢውን መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ፤

ረ. የማኅበሩን ሠራተኞች ወይም በማኅበሩ የታዘዙ ሌሎች ሰዎች የመስኖ መስመሩን የኦፐሬሽንና ጥገና ሥራ ለማካሄድ እንደአስፈላጊነቱ መኪናዎችን ወይም መሣሪያዎችን ይዘው ሲሄዱ ወደ መሬቱ እንዳይገቡ የከለከለ ከሆነ፤ወይም



# PART TWELVE

## Miscellaneous Provisions

### 60. Administrative Sanctions

1. The association may impose administrative sanctions against a member who fails to:

a. Observe the by laws or any internal regulations adopted by the general assembly of the association;

b. Pay timely any charges determined in accordance with the by-laws and this proclamation or to provide labour service whenever necessary;

c. use irrigation water in accordance with the association's watering schedule;

d. pay the repair or replacement costs of any property or equipment of the association damaged as a result of his negligent or intentional act;

e. provide relevant information to the association about his use of land or water;

f. allow employees of the association or other Persons ordered by the association to enter his land , with cars or equipments as necessary , in order to undertake works concerning the operation and maintenance of the irrigation system; or

ሰ. የመስኖና ድሬኔጅ አውታሩን ኦፕሬሽን የሚመለከቱ ቴክኒካዊ ደንቦችን ለማክበር ፈቃደኛ ካልሆነ ማኀበሩ አስተዳደራዊ ቅጣቶችን ሊጥልበት ይችላል፡፡

2. የቅጣቱ አይነትና መጠን በእያንዳንዱ ማኀበር መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ሲሆን በዋናነት የገንዘብ ወይም የመስኖ ዉሀ አቅርቦትን ጨምሮ አገልግሎትን ማቋረጥ ሊሆን ይችላል፤

3. ቅጣቱ የሚጣለው በሥራ አመራር ኮሚቴው ሲሆን ለክርክር አወሳሰን ኮሚቴ ይግባኝ ሊቀርብበት ይችላል፡፡

## 61. ቅጣትን ለማስፈፀም የሌሎች አካላት ትብብር

ጥፋት በፈፀመው አባል ላይ የተጣለውን ቅጣት የወረዳና የቀበሌ አስተዳደር የሥራ ኃላፊዎች የማስፈፀም ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## 62. ማህበራት ከአካባቢ አስተዳደር አካላት ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት

1. በክልል፣ በዞን፣በወረዳና በቀበሌ ደረጃ የሚገኙ የስራ ኃላፊዎች ከማኀበራቱ የሥራ አመራር ኮሚቴዎች የጽሁፍ ጥያቄ ካልቀረበላቸው በስተቀር ማኀበራቱ በሚቋቋሙበት ጊዜም ሆነ ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት ጣልቃ መግባት የለባቸውም፤

2. የወረዳና የቀበሌ አስተዳደር መዋቅሮች በሥልጣን ክልላቸው ውስጥ ለሚገኙ ማኀበራት የአሰራር ነፃነታቸውን በማክበር ለሥራ እንቅስቃሴያቸው ተገቢነት ያለውን ድጋፍ መስጠት አለባቸው፤

g. Comply with applicable technical rules concerning the operation of the irrigation and drainage system.

2. The type and amount of sanction shall be specified in the by-laws of each association and in particular it could be fine or the suspension of the provision of services including the supply of irrigation water;

3. A sanction shall be imposed by the management committee, and an appeal against such sanction may be submitted to a dispute settlement committee.

## 61. Cooperation of Other Organs for Enforcement

The woreda and kebele administration officials shall have a responsibility with regards the enforcement of sanctions against a defaulting member.

## 62. Relationship of Associations with Local Administrations

1. Officials of the region, zone, woreda and kebele may not interfere in the affairs of an association during the formation of association or in the function of the association after its formation, unless there is a written request of the management committee;

2. The woreda and kebele administrations shall provide support necessary for the operation of associations within their jurisdiction by respecting their autonomy;

3. የአንድ ማኅበር የአገልግሎት ክልል የውሃውን የተፈጥሮ አወራረድ ተከትሎ ከአንድ ዞን፣ወረዳ ወይም ቀበሌ አስተዳደር ወሰን ወደ ሌላው ዞን፣ወረዳ ወይም ቀበሌ አስተዳደር ወሰን የሚሻገር ከሆነ ከእያንዳንዱ አስተዳደር አካል የሚወከሉ አባላት ያሉበት ኮሚቴ የማኅበሩን ጉዳይ በተመለከተ ከአስተዳደር መዋቅሩ ጋር አገናኝ ሆነው ይሰራሉ፡፡

## 63. ስለ ክልሉ መንግስት ድጋፍ

በዚህ አዋጅ ውስጥ የተመለከቱት የሌሎች አካላት ድጋፎች እንዲሁም በኢንቨስትመንትና በሌሎች ሕጎች የተፈቀዱት ማበረታቻዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋሙት ማህበራት ተፈፃሚ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ማኅበራቱ የሚከተሉትን ተጨማሪ ድጋፎችና ማበረታቻዎች በተለየ ሁኔታ ያገኛሉ፦

1. ከገቢ ግብር ክፍያ ነፃ መሆን፣
2. ለስራ የሚያስፈልጋቸውን መሬት በነፃ ማግኘት፤
2. እንቅስቃሴያቸውን የሚረዱ ስልጠናዎችንና ሙያዊ ድጋፎችን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ማግኘት፤
4. በሚገጥማቸው የፍትሃብሄር ክርክር ከሚከፈል የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ነፃ መሆን፤
5. ከክልሉ ፍትህ ቢሮና ከተዋረድ አካላቱ በኩል ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት ማግኘት።

3. If the service area of the association transcends from one zone, woreda or kebele administration to another zone, woreda or kebele administration following the natural flow of the river, there shall be delegated committee members from each administration to communicate the affairs of the association with the local administrations.

## 63. Support of the Regional Government

Other organs supports, specified in this proclamation, as well as, incentives allowed with investment and other laws, without prejudice to the applicability of the established associations pursuant to this proclamation, the associations shall get the following additional supports and incentives:

1. Free from income tax payment;
2. Get free of land necessary for works;
3. Get trainings and professional supports from the pertinent bodies that shall help their activities;
4. Free from the jurisdiction activity payment on the civil dispute case;
5. Get free the legal supporting service from the regional justice bureau and its subordinates.

## 64.የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. ቀደም ሲል በክልሉ ውስጥ በህብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ መሠረት በተለያየ ጊዜ የተቋቋሙ የመስኖ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ የመስኖና ድሬኔጅ ውኃ አውታር ሥራዎችን እንዲሰሩ በዚህ አዋጅ መሠረት የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት ሆነው ይቋቋማሉ፤
2. የመስኖና ድሬኔጅ ሥራ ሲያካሂድ የነበረ ማናቸውም የኅብረት ሥራ ማኅበር የመስኖና የድሬኔጅ ውሃ አውታር ሥራዎችን የሚያካሂድና ኃላፊነት የሚቀበል ማኅበር ስለሚመሠረትበት ሁኔታ ድጋፍ ይሰጣል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት አንድ ማኅበር ከተመሰረተ በኋላ ድጋፍ ሲሰጥ የነበረው ነባሩ የመስኖ ኅብረት ስራ ማኅበር፡-

ሀ. በመስኖና ድሬኔጅ አውታሩ ላይ ያሉትን መብቶቹንና ግዴታዎቹን አዲስ ለተመሰረተው የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበር በነፃ ያስተላልፋል፤

ለ. ለመስኖና ድሬኔጅ አዉታሩ ከመስኖ ዉኃ ተጠቃሚዎች ለጥገናና ሥራ ማስኬጃ የተሰበሰበና የተጠራቀመ ገንዘብ ካለ አዲስ ለተመሰረተው የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበር ገቢ ያደርጋል፤

ሐ. አዲስ ከተመሠረተው የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበር ጋር በማኅበሩ አገልግሎት ክልል ውስጥ ለሚካሄድ የመስኖ ግብርና ድጋፍ ለማድረግ በትብብር ይሠራል።

## 64. Transitory Provisions

1. The irrigation cooperative societies established with different times, pursuant to cooperative societies proclamation previously in the region, pursuant to this proclamation shall be established as the irrigation water users' associations to work the irrigation and drainage water system activities within two years starting from the effective date of this proclamation;
2. Every cooperative society which had been operating the irrigation and drainage system shall support the formation of irrigation water users' association to take responsibility for the irrigation and drainage system;
3. Following the formation of association pursuant to sub-artcle (2) of this Article , the existing irrigation cooperative society which had been supporting the formation of association shall:

a. Gratuitously transfer the rights and duties of the former irrigation and drainage cooperative society to the newly formed of the irrigation water users association;

b. If there is a deposited money, for the maintenance and operational service budget from the irrigation water users' to the irrigation and drainage system, shall be transferred to the newly formed irrigation water users' association;

c. Cooperate with the newly formed irrigation water users' association in order to support irrigated agriculture within the service area of the association.

## 65. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 66. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

1. የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፤
2. ቢሮው ይህንን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 67. አዋጁ የሚፀናበት ቀን

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህርዳር

……. 2008 ዓ.ም

ገዱ አንዳርጋቸው

የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዝዳንት



## 65. Inapplicable Laws

Any law, regulation, directives or customary practice inconsistent with this proclamation shall not be applicable on matters provided in this proclamation.

## 66. Power to Issue Regulations and Directives

1. The regional government council may issue regulations necessary for the implementation of this proclamation;
2. The bureau may issue directives necessary for the implementation of this proclamation and regulations to be issued with this proclamation.

## 67. Effective Date

This proclamation shall come into force as of the date of its official publication on the Zikre-Hig Gazzeettee of the Regional State

**Done at Bahir Dar,**

**This th Day of ………, 2016**

**Gedu Andargachew**

**President of the Amhara National Region**